ምዕራፍ ዘጠኝ

ከቤተሰብ ጋር የተያያዙ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች

ወላጅ ከመሆን ጋር ተያይዘው የሚመጡ ብዙ ተግዳሮት፥ አነጋጋሪ ጉዳዮች እና ልዩ ትኩረት የሚጠይቁ በርካታ ነገሮች እንዳሉ ከልምምድ የም ናውቀው እውነት ነው። ከእነዚህም መካከል ልጆች የማሳደግ፥ ዘዴ፥ ነጠላ ወላጆች (single parents) የሚጋፈጧቸው ችግሮች፥ ልጆችን የመቅጣት አነጋ ጋሪ ጉዳይ እና በጋብቻና በቤተሰብ የሚመጣ መንፈሳዊ ውጊያ ይገኙበታል።

ሀ. በዚህ ዘመን ወላጅ ልጆችን የማሳደግ ጉዳይ፥

በዘመናችን ወላጆች ልጆቻቸውን እንዴት አድርገው ማሳደግ እንዳለባ ቸውና ምን ዓይነት የዲስፕሊን መንገድ መጠቀም እንዳለባቸው የሚያመለክ ቱ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ መጻህፍቶች ተፅፈዋል።[50] ወላጆች የተወሰነ የዲስፕሊን አሰጣጥ መንገድ መያዛቸው የተለያዩ ጥቅሞች አሉት። አንደኛ ወላጆች የያዙት የዲስፕሊን መንገድ መኖሩ በወላጆች ላይ የተለየ እርግጠኝ

[50] ለምሳሌ፦ Gary Ezzo and Anne M. Ezzo, *Growing Kids God's Way: Biblical Ethics for Parenting*, 4th ed. (Chatsworth, CA: Growing Families International, 1997); and Tedd Tripp, *Shepherding a Child's Heart*, (Wapallopen, PA: Shepherd, 1998).

ነት ከመስጠቱም ሌላ፤ የወላጅነት ዓላማና ጥላን እንዳላቸውና እንደሚሰማቸ ው ያሳያል። ሁለተኛ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት የታወቀና የማይለዋወጥ እንዲሆን ይረዳል። ሦስተኛ ወላጆች የሚያምኑበት የዲስፕሊ ን አሰጣጥ ዘዴ መያዛቸው ተመሳሳይ የዲስፕሊን መንገድ ከሚጠቀሙ ወላ�ጆ ች ጋር ግንኙነት ለመፍጠርና ለመመካከርም ይረዳቸዋል።

በእንጻሩም የተወሰነ የዲስፕሊን አሰጣጥ ዘዴ መያዙ የራሱ የሆኑ ችግ ሮችም አሉት። አንደኛ እንዲህ ዓይነት የተወሰነ ግትር ዘዴ (rigid method) መጠቀማቸው በልጆቻቸው ላይ ብዙ አሳሳቢ ችግሮች ቢያመጣም÷ ሁሉ "ትክክልና መልካም" እንደሆነ በማሳየት የውሸት ጸጥታ (false security) ሊሰ ጣቸው ይችላል። ሁለተኛ የተወሰነ ዘዴ መጠቀም፤ የልጆቻቸውን ሰብዓዊ ክብር በመጠበቅ ሊመሯቸው ሲገባ÷ በማይጨበጥ የዲስፕሊን መመሪያ (abstract principles of discipline) ላይ እንዲያተኩሩ ያደርጋቸዋል። ሦስተ ኛ እንዲህ ዓይነት ግትር ዘዴ (rigid method) የእያንዳንዱ ልጅ ግላዊ አፈጣ ጠርና (individuality) ልዩ ስብዕና (personality) ግምት ውስጥ ስለማያስገባ፣ ምንም እንኳን ልጆች ዲሲፕሊን መደረግ እንዳለባቸው ቢታወቅም÷ ወላጆች የዲስፕሊን ዘዴውን በሥራ ሲተረጉሙት ግን ፍትህ በሳደለው መንገድ እን ዲያደር ጉት ያስገድዳቸዋል።

የእያንዳንዱ ልጅ አፈጣጠርና ስብዕና የተለያየ ስለሆነ እንደ አፈጣጠ ራቸውና ባህሪያቸው የተለያዩ የዲስፕሊን መንገዶች÷ በተለይም በእግዚአብ ሔር ቃል የተለወሱና የልጆችን ስብዕና ክብር የሚጠብቁ ሊሆኑ ይገባቸዋል። እንዲህ ዓይነት መንገዶችን ለማጤን የእግዚአብሔር ቃል ብስለት÷ የመንፈ ስ ቅዱስ ሙላት ፍሬዎችና ምሪት÷ የእግዚአብሔርም ሰዎች ምክር እንደዋና ማጣቀሻዎች (references) ልንወስዳቸው ይገባል። በዚህም ውስጥ ወላጆች ለልጆቻቸው የማይለዋወጥ ፍቅር፤ መንፈሳዊ እንክብካቤና÷ ዲስፕሊን ሊሰጧ ቸው ያስልጋል። (ኤፌ 6÷4 ፤ 2ጴጥ 3÷18) በእንጻሩም ወላጆች ራሳቸውም ሆነ ልጆቻቸው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ÷ የከበረ ስብዕና ያላቸውና

መልካም ነገር ለማድረግ የሚችሉበት አቅም (potential) ያላቸው መሆናቸውን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአዳም የኃጢአት ውድቀት ምክንያትም የወደቁ ፍጥረቶች (fallen nature)፤ በውስጣቸው ያለው የዋጋ አሰጣጥ ሚዛን (value system) የተዛባ የተጐበጠረበረና (marred)÷ ክፉ የሆነ ነገር ለማድረግ የሚችሉበት አቅም ያላቸው መሆኑን በሚገባ ሊያውቁና ሊያጤኑት ይገባቸዋል። በተጨማሪም ወላጆች ልጆቻቸው ሊታዘቧቸው ባይፈልጉ በአደባባይ በእነሱ ላይ ኃፍረት ስለሚያመጣ ነው? ወይንስ ልጆቻቸው በትምህርታቸው በጣም ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ የሚፈልጉት ለራሳቸው ክብር ስለሚያመጣ ነው? ወይ ስ ልጆቻቸው የሚመርጡት የትምህርትና የሥራ መስክ (profession) ዓይነት ÷ (ለምሳሌ:- ህግ÷ ህክምና መሃንዲስነት እና የሚመርጡት የትዳር ጓደኛ የኑሮ አቋም ለራሳቸው ለወላጆች በህብረተ-ሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት (social acceptance) ነው? ወይንስ የልጆቻቸውን የትምህርት ዓለም ሲወስኑ ለልጆቻቸው ጥቅም ሳይሆን ለራሳቸው ምኞት ሲሉ ነው? የሚሉት መሠረታዊ የሐሳብ መነሻ ጥያቄዎች ፊት ለፊት ሊጋፈጡዋቸው የሚገቡ ጥያቄዎች ናቸው።[51]

1. ብቸኛ/ ነጠላ/ ሌላ ወላጆች÷ (Single Parents)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቸኛ/ነጠላ ወላጅነት (single parenting) በእግዚአብሔር የመጀመሪያ ዓላማ ውስጥ የነበረ አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል ስናጠና ሁለት ዓይነት ብቸኛ ወላጅነት ሲገለጽ እናያለን። አንድም አባት የሌላቸው ልጆች (orphans) ጉዳይና፣ ባሎቻቸው ስለሞቱባቸው (widows) እግዚአብሔር እንደሚገደውና እንደሚራራ ይናገራል። ነገር ግን ብቸኛ/ነጠላ ወላጅነት በፍቺና ትዳርን በማፍረስ ምክንያት ሲመጣ ግን የተለየ ትኩረትና ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። ይህ የሚያመለክተው ሳይጋቡ ወይም ከተጋቡ

[51] ልጆችን በማስተማር ጉዳይ ለማየት የሚከተለውን መጽሐፍ ማንበብ ይችላሉ:- William A. Strange, *Children in the Early Church: Children in the Ancient World, The New Testament, and the Early Church*, (Carlistle, U.K.: Paternoster, 1996), 80-81.

በኋላ "በተለያየ ምክንያት" ከተፋቱ በኋላ የተወለደውን ልጅ ለማሳደግ ህጋዊ መብት (legal custody) የተሰጠውን ወንድ ወይንም ሴት ያመለክታል::[52]

ወላጆች በፍቺ ምክንያት ትዳራቸውን ሲያፈርሱና አብረው መኖር ሳይችሉ ሲቀሩ ዓይነታቸው ብዙ የሆኑ ችግሮችን ያስከትላል:: ልጆች ወላጆቻቸው ሲፋቱ የውስጣቸው ስሜት ይቀደዳል (emotionally torn apart)፤ ይህም ሁኔታ የልጆችን ሥነ-ልቦናዊ ዕድገት (psychological development) ከማጨናገፉም በላይ፤ ልጆቹም በእነሱ ምክንያት ወላጆቻቸው እንደተፋቱ ስለሚመስላቸው አላስፈላጊ የሆነ የህሊና ወቀሳ ያስከትልባቸዋል::[53]

እግዚአብሔር ወላጆች የሌላቸውን ልጆች እና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን መበለቶች አይቶ እጅግ እንደሚገደውና ስለ እነርሱም እንደሚሟገት ብቸኛ/ ነጠላ/ ሌላ ወላጆችም ራሳቸውም ይሁን ሌላው የትዳር ጓደኛ ባመጣው ሰበብ የመሳው የመከራ ጫና ጫንቃቸውን ሲያሳብጠው አይቶ የሚራራ፥ ፈጽሽታቸውንም የሚያደምጥ፥ የምህረት እጁንም የሚዘረጋ አምላክ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አባት ለሌላቸው ልጆች አጋዥ፤ (ዘዳ 10÷18፥ 27÷19፤ መዝ 10÷18፤ 82÷3)÷ ረዳት (መዝ 10÷14÷ 146÷9)÷ አባትም (መዝ. 68÷5) እንደሆነ ተገልጿል::[54] እንደዚሁም የእግዚአብሔር ህዝብም አባት ለሌላቸው ልጆችና ለብቸኛ ወላጆች እንዲህ ዓይነት ርኅራኄ ሊያሳዩ ይጠበቅ

---

[52] ለሰፊ ውይይት የሚከተለውን መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል:- Alice b. Tolbert, "The Crisis of Single Parent Families," *Urban Mission* 7 (1989): 9-15.

[53] ለሰፊ ውይይት የሚከተለውን መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል:- Don E. Eberly, "The Collapse and Recovery of Fatherhood," in Don E. Eberly, ed., *The Faith Fact in Fatherhood: Renewing the Sacred Vocation of Fathering*, (Lanham, MD: Rowman & Littlefield, 1999): 4-20; Rob Palkovitz, *Involved Fathering and Men's Adult Development: Provisional Balances*, (Mahwah, N.J.: Lawrence Erlbaum Associates, 2002; and Paul C. Vitz, *Faith of the Fatherless: The Psychology of Atheism*, (Dallas: TX: Spence, 1999).

[54] ለሰፊ ውይይት የሚከተሉትን መጣጥፍ ማንበብ ይቻላል:- Charles Fensham, "Widow, Orphans, and the Poor in Ancient Near Eastern Legal and Wisdom Literature," *Journal of Near Eastern Studies* 21 91962): 129-139; Harold V. Bennett, *Injustice Made Legal: Deutronomic Law and the Plight of Widows, Strangers, and Orphans in Ancient Israel*, (Grand Rapids, Michigan: Eerdmans, 2002).

ባቸዋል::[55] ነቢያትም በዚህ ጉዳይ ላይ የማስጠንቀቂያ መልዕክቶችን ያስተላልፉ ነበር:: (ኢሳ 1÷23 ፤ ኤር 5÷28 ፤ 7÷6 ፤ ሆዘቅኤል 22÷7 ፤ ዘካ 7÷10 -14 ፤ ሚል 3÷5) ያዕቆብም በመልዕክቱ ይህንን የሚመስል መልዕክት አስተላልፏል:: (ያዕ 1÷27)

ቤተክርስትያን በአሁኑ ዘመን ያለውን ሸክም በማቅለል ብቸኛ/ ነጠላ ወላጆችን ልትረዳበት የምትችልበት አገልግሎት መኖር አለበት::[56] ከዚህም በላይ ቤተክርስትያን የብቸኛ/ ነጠላ ወላጆች (single parents) ሰብዓዊ ክብር በሚጠብቅ መልኩ ለነሱ በመራራት በማስተዋልና በርኅራኄ ችግራቸው የሚቀረፍበትን መንገድ በመተለም የትዳር ጓደኛቸው የፈጠረውን ክፍተት በመሙላት በምክር÷ በፀሎት÷በገንዘብና በየጊዜው በመጎብኘትና አብሮም በመቆም፤ ድጋፍ የሚሆኑ ቤተሰቦችንም በማዘጋጀት (support group) ልዩ አገልግሎት ማካሄድ ከጌታም ሆነ ከሰው ይጠበቅበታል::[57]

2. የቅጣት/ዲሲፕሊን ጉዳይ÷ (Physical Discipline)

ወላጆች ልጆቻቸውን ለመቅጣት በሥጋቸው ላይ የሚደረግ ቅጣት (physical punishment) አግባብ ያለውና የሚገባ ለመሆኑ በዚህ ዘመን ብዙ የሚያነጋግር ጉዳይ ሆኖአል:: የመነጋገሪያ ሃሳብ የሆነው በመጽሐፈ ምሳሌ

---

[55]ዘዳግም 24÷17፤ 27÷19፤ መዝ. 23÷10፤ ኢሳ. 1÷17፤ ኤር. 7÷6፤ 22÷3፤ ዘካ. 7÷10፤ ዘፅ. 26÷12.

[56]ለበፊ ውይይት የሚከተሉትን ይመልከቱ÷ Blake J. Neff, "The Diverse Traditional Family," in Blake J. Neff and Donal Ratcliff, eds., *Hand Book of Family Religious Education*, (Brimingham: Religious Education Press, 1995): 121-124; Jane Hannah and Dick Stafford, *Single Parenting with Dick and Jane: A Biblical, Back-to-Basics Approach to the Challenges Facing Today's Single Parent*, (Nashville, TN: Family Touch, 1993); Ramona Warren, *Parenting Alone, Family Growth Electives*, (Elgin, ILL.: David C. Cook, 1993); Robert G. Barens *Single Parenting*, (Wheaton, ILL.: Tyndale, 1992); Greg Cynaumon, *Helping Single Parents with Troubled Kids: A Ministry Resource for Pastors and Youth Workers*, (Colorado Springs, CO: NavPress, 1992); David Blackwelder, "Single Parents: In Need of Pastoral Support," in *Clinical Handbook of Pastoral Counseling*, vol. 2 (Mahwah, NJ: Paulist, 1993): 329-359.

[57]ለበፊ ውይይት የሚከተለውን መጣጥፍ መመልከት ይቻላል÷ Susan Graham Mattis, "Good Samaritans for Single Parents," *Focus on the Family* (April 2004): 20-21.

የተጠቀሰው ልጅን "በበትር" የመቅጣት ጉዳይ ነው። በዚህ መጽሐፍ ላይ እን ደተገለጸው ልጅን "በበትር" መምታት/ዲሲፕሊን ማድረግ ሦስት መሰረታዊ ጥቅሞች እንዳሉት ተጠቅሷል፦ ወላጆች ለልጆቻቸው ያላቸውን ፍቅር መግለ ጫ ሆኖ (ምሳሌ 13÷24)፥ ልጆችን ከስህተት አሰራር ለመጠበቅና ጥበብን እን ዲያገኙ ለማድረግ፥ ወይም በእግዚአብሔር ፍርሃት እንዲያድጉ ለማድረግ (ምሳሌ 22÷15 ÷ 29÷15) ለልጁ ደህንነት ሲባልም (ምሳሌ 23÷13-14)። በሌላ በኩልም "በትር" ሞኞችን ለመቅጣት ወይም ለማረም የሚደረግ እንደ ሆነም ተገልጿል። (ማሳሌ 10:13 ፤ 14:3 ፤ 22:8 ፤ 26:3)

- በአሁኑ ዘመን ልጅን መምታት በአጠቃላይ በአውስትራሊያ፥ ክሮኤሽያ፥ ላትቪያ፥ ኖርዌይ ፥ ስዊድን ፥ ዴንማርክና ፊንላንድ በህግ ተከልክሏል፡ ፡ ልጅን መምታት (በዲሲፕሊን መልክ) በካናዳ ፥ በእንግሊዝ፥ ጀርመን፥ ጣልያን፥ ቤልጂየም፥ ቡልጋሪያ፥ እና አየርላንድ ለመከልከል እየተዘጋ ጁ ነው። የተባበሩት የዓለም መንግሥታትም (United Nations) መንግሥ ታት በየአገሮቻቸው ልጅን ዲሲፕሊን ማድረግ እንዲያስቀሩ ከፍተኛ ጫና እየፈጠሩባቸው ነው።[58] ልጆችን በስጋ መቅጣት (Physical Punish ment) በሦስት ምክንያቶች/ አቅጣጫዎች ይወቀሳል። ልጅን በዲሲፕሊን መምታት ልጁን ያለአግባብ መጉዳት (Physical abuse) ጋር ተደርጎ መ ወሰዱ፤ ልጅን በሥጋ መቅጣት በልጁ ላይ የሥነ-ልቦና ጉዳት (Psycholog ical Damage) ተደርጎ ስለሚወሰድ፤ በብሉይ ኪዳን የነበረው ሐሳብ በአዲ ስ ኪዳን ቀጣይነት ስለሌለው (Discontinuity between the Old and New Testaments in relation to the child discipline)። ከዚህም የተነሣ ልጅን መቅጣት (physical discipline) ልጁን በሥጋ ከመጉዳት ጋር (physical abuse) እኩል ተደርጎ በመወሰዱ በሰብዓዊ መብት አስጠባቂ ድርጅት በ1979 "ዓለም አቀፍ የልጆች ዓመት" ("International Year of the Chil

[58] ልጅን ድስፕልን በማድረግ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ለማንበብ የሚከተለውን ማንበብ ይቻላል፥ R. Albert Mohler, Jr. "Should Spanking Be Banned? Parental Authority Under Assault," 6/22/2004, at http://www.crosswalk.com/news/weblogs/mohler/126921.html.

ፊ") ተደርጎ ተወሰደ::[59] በዚህ ጊዜ የተነሳው የመብት ጉዳይ "ከፍርሃትና በሥጋ የሚደረግ አግባብ ከሌለው የቅጣት መንገድ ሁሉ ነፃነት" ("freedom from fear or physical harm and abuse") የሚል ነበር::[60] በተጠማሪም አስተርሁስ (Oasterhuis) የምትባለዋ የሥነ ልቦና ምሁር ቫን ሊኡወን (Van Leeuewen) የሚባለውን ሰው በመጥቀስ የሚከተለውን ሐሳብ አስፍራለች÷ "ምንም እንኳን የዝሙት ወንጀልና በቤተሰብ ላይ የሚደረግ የአመፅ ሥራ ስምንት ከመቶው የሚካሄደው በመጠጥ ሱስ በተያዙ ቤተሰቦች መካከል ቢሆንም፣ እነዚህ ሁለቱ ድርጊቶች ግን በመጠጥ ሱስ ከተያዙት ባላነሰ ደረጃ ከፍ ያለ የሐይማኖት እምነት ባላቸውም ቤተሰቦች ይካሄዳሉ::" "Although eight percent of sexual Abuse and family Violence occurs in alcoholic families, the next highest incidence of both abuses takes place in intact highly religious homes."[61]

ይህም ማለት ልጅን በምንም ዓይነት ቅጣት (Physical discipline) በሥጋ ከመጉዳት ጋር (Physical Abuse) የተያያዙ ተደርጎ ተወስዷል::[62]

- ሁለተኛ ልጅን መቅጣት/ ዲስፕሊን ማድረግ በልጆች ላይ የሥነ-ልቦና ጉዳት (Psychological Damage) ተደርጎ የመወሰድ ጉዳይ ነው:: አስተር ሁስ (Oasterhuis) እንዲያውም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረውን ህብረተ-ሰብ በመግለፅ እንዲህ ብላ ፅፋለች:: "በጥንት ዘመን የነበሩት ህጎች በሥጋ ላይ የሚደረጉ ቅጣቶችን የሚያበረታታ ስለነበር፣ በወላጆችም ሆነ÷ በግ

[59] Alyce Oasterhuis, "Abolishing the Rod," *Journal of Psychology and Theology* 21, no. 2 (Summer 1993):132.
[60] Ibid.
[61] Mary S. Van Leeuwen, *Gender and Grace* (Downers Grove, IL: InterVarsity Press, 1990), 170; Quoted also in Oasterhuis, "Abolishing the Rod," 131.
[62] ለለፈ ውይይት የሚከተለውን ማንበብ ይቻላል÷ Virginia R. Mollankott, "Gender, Ethics, and Parenting," Review of the Case Against Spanking: How to Discipline Your Child Without Hitting, by Irwin A. Hyman, *The Witness* (April 2000): 17-19.

ዝምችም ዘንድ በፈለጉት ሰው ላይ ጠባይ ለማረሚያ በሥጋ ላይ የሚደረግ ሥቃይ በነፃነት መፈፀም የተለመደ ነበር::" "Because ancient laws implemented severe physical punishment for infractions, physical pain was freely used by parents and masters to correct misbehavior."[63]

ስለዚህም በእርሷ አባባል ህብረተ-ሰቡ ለልጆች የተለየ አክብሮት ስላለው ምንም የሥጋ ቅጣት/ዲሲፕሊን ተቀባይነት የለውም ትላለች:: አሊስ ሚለር (Alice Miller) የምትባል ሊላዋ የሥነ-ልቦና ምሁር (Psychologist) በሥጋ የሚደረግ ቅጣት ከፍተኛ የሆነ የሥነ-ልቦና ጉዳት (Phsychological Trauma) ከማምጣቱም በላይ፥ የነርቭ ግኝት (Finding) እንዲህ በሚል ትጠቅሳለች፥ "በብዙ ሥቃይና በብዙ ግፍያ የተጣሉ ልጆች መካከል ሰላሳ ከመቶዎቹ በሰው አዕምሮ ውስጥ ያሉትን የስሜት ህዋሳቶቻችንን የሚቆጣጠሩት ክፍሎች እንደተጎዱባቸው ያሳያሉ::" "Have estabilished that traumatized and neglected children display severe lesions affecting up to 30 percent of those areas of the brain that control our emotions."[64]

በተጨማሪም አሊስ ሚለር (Allice Miller) በቀድሞ ዘመን በአመራራቸው በአለም ላይ ይህ ነው የማይባል ጉዳት ያመጡትን ሒትለርና ሙሶሎኒ በልጅነታቸው ወላጆቻቸው አግባብ በሌለው ሥጋዊ ቅጣት (Physical Abuse) ያሳደጓቸው በመሆናቸው እንደሆነም ትገልፃለች::[65]

- ሦስተኛው ተቃውሞ በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ክፍተት (Discontinuity) መኖሩን መሠረት ያደረገ ነው:: ይህ አስተሳሰብ አዲስ ኪዳን

[63]Oasterhuis, "Abolishing the Rod," 128.
[64]Alice Miller, "Against Spanking," *Tikkun* 15, no. 2 (March/ April 2000): 17-19.
[65]Ibid., 18.

የብሉይ ኪዳን እውነታ (Reality) በመሆኑ፤ የልጅን አቀጣጥ discipline) በተ መለከተ በቅድሚያ ሊታይ ይገባዋል ብሎ ያምናል።[66]

ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረው አገልግሎት ለልጆች ያሳየው ልዩ አቀባበልና ስለ ልጆች ያለው ልዩ አመለካከት የእኛንም አቀባበል ፣ አመለካ ከትና ግንኙነት ሊቀርፀው ይገባል። ኢየሱስ በቃልም ሆነ በሥራ (Word And Deed) በትምህርቱም ሆነ በግንኙነቱ በብሉይ ኪዳን የነበረው አሉታዊ ተጽዕ ኖና (Negative Attitude) በሴቶችና በልጆች ላይ የነበረውን ዝቅተኛ አመለካ ከት በአዲስ ኪዳን ክብራቸውን በሚጠብቅ መንገድ እንዳደሰው ስናይ ፣ ሴቶ ችና ልጆች እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን የአይሁድ ሕብረተሰብ አስተሳሰብ በሁ ለተኛ ደረጃ የሚታዩና ሥፍራ ሊሰጣቸው የማይገባ እና በንብረትነት የሚታ ሰቡ (የወንዶች Commodity)፤ ይሆኑ የከበሩ፥ ትልቅና የከበረ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉና የሚገባቸው እንደሆነ በሚገባ ገልፆታል። ስለዚህም ይህን የአዲስ ኪዳን እምነት የአመለካከት ለውጥ ልብ ሊሉ ይገባቸዋል። በሌላ በኩል ደግ ሞ አግባብ የሌለው የሥጋ ቅጣት (physical abuse) በአዲስ ኪዳን ያለው ሥነ-መለኮታዊ እምነትና የዘመኑም ህብረተሰብ በፍፁም ባይደግፈውም፤ ይህ ማለት ልጅን ፈጽሞ ዲሲፕሊን ማድረግ አይቻልም ወይም አያስፈልግም ማለት ግን አይደለም።[67] አለአግባብ የሚደረግ ቅጣት (Physical Abuse) በፍቅርና በዓላማ ልጁን ለመምራት የሚደረግ የዲሲፕሊን መንገድ (Spankin g) የሚከለክል እንደሆነ ምንም አይነት መረጃ የለም።[68] ልጆች በመልካም ሁኔታና እግዚአብሔርንም በመፍራት እንዲያድጉ ካስፈለገ ላደረጉት ስህተት ወይም ጥፋት የሚያስከትል ሰበብ እንዳለ ማወቃቸውና ከዚያም ከፍቅርና

---

[66] ለሰፊ ውይይት የሚከተለውን ማንበብ ይቻላል፥ Kenneth O. Gangle and Mark F. Rooker, "Response to Oosteruis: Discipline Versus Punishment," "*Journal of Psychology and Theology* 21, no. 2 (Summer 1993): 135.

[67] የወላጆች ልጅን የመቅጣት ህጋዊነት የሚከተለውን ይመልከቱ፥ Child Protection Reform, "Spanking as a Discipline, not abuse," http://www.childprotectionreform.org/policy/spanking_home.html.

[68] Robert E. Lazrelere, "Response to Oasterhuis Empirically justified uses of Spanking: Toward a Discriminating View of Corporal Punishment," *Journal of Psychology and Theology* 21, no. 2 (1993): 142-147.

ዓላማ ካለው ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ የሚደረግ ዲሲፕ ሊን እንዲቀበሉ ማድ ረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ሆኖም ወላጆች የዲሲፕሊን መንገዶችን በሚጠ ቀሙበት ጊዜ በቅድሚያ የራሳቸውን ስሜትና ባህርይ መቆጣጠር፤ ልጆቻቸ ውን የቁጣቸው መወጣጫ አለማድረግና፤ የእያንዳንዱም ልጅ ልዩ ስብዕና (unique personality) ባህርይና (Temperament) የእድገት ደረጃ ግምት ውስ ጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

ከዚህም በተጨማሪ አንድ አይነት የቅጣት መንገድ መጠቀሙ ስለማ ይረዳ የተለያዩ የዲሲፕሊን መንገዶችን እንደየሁኔታውና እንደ እድሜያቸ ውም ደረጃ መጠን በማስተዋል መጠቀሙ በጣም አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ÷

- ከስህተታቸው እንዲታረሙ "ጉቦ" ከመስጠት ይልቅ÷ ያጠፉትን ጥፋት ካስተካከሉ በኋላ "ሽልማት" (Reward) መስጠት፤
- ለተወሰነ ጊዜ ክፍላቸው ውስጥ እንዲቀመጡ ማድረግ (Timeout)
- ያገኙት ከነበረ ጥቅም እስኪታረሙ ድረስ ለተወሰነ ጊዜ መከልከል (Grounding)
- የግል ኮንፈረንስ (Personal Conference)
- አብሮ በመጓዝ መመካከር (walk and talk)
- መደማመጥ በሞላበት ሁኔታ መነጋገር (Dialogue, and not monologue)
- ምክር መስጠትና መመሰኑና በሥራ መተርጎሙን ለልጆቹ መተው፤ ወዘተ

ለ. የወላጆችና የልጆች ግንኙነት÷

1. የወላጆችና የልጆችን ግኑኝነት የሚያፈርሱ÷

(ኤፌ 6:1-4፤ ቆላ 3:20-21፤ 1ጢሞ 3:4፤12፤ ምሳሌ 20:7፤ 22:6፤ 23:13-14፤ 24 ፤ 28-70፤ 29:15 ፤ 30:17፤ ኢሳ 8:18)

- ልጆችን ያለልክ ማመስገን÷
- ልጅን የቁጣችን መወጣጫ ማድረግ÷ (መዝ 27:10 ፤ 1ሳሙ 16:6-13)
- ባልና ሚስት በልጆች ፊት ስሜትን ሳይቆጣጠሩ መጨቃጨቅ÷
- በትዳር ዓለም ምንም ችግር እንደሌለ አድርጎ በማሳየት የለበጣ ኑሮ መኖር÷
- ልጆችን በማበላለጥ አድልዎ በሞላበት መንገድ መውደድ÷
- ልጆችን የገንዘብ ጫና ምክንያት እንደሆኑ አድርጎ መቁጠር÷
- አግባብ በሌለውና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ የዲሲፕሊን መንገዶችን መጠቀም÷
- ልጆችን ከጥፋታቸው እንዲመለሱ ከማድረግ ይልቅ ቢያደርጉት ወሮታ (Reward)
  እንደሚሰጣቸው መናገር÷
- ለልጆች ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ዘይቤዎች (Value System) ማሳየት ወይም መስጠት÷
- በውሳኔ አሰጣጣችን በተለይም የሞትና የህይወት ለሆኑ ጉዳዮች ላይ የጸና አቋም አለማሳየት (Consistency ማጣት)÷
- ሊለወጡ በሚችሉ ጉዳዮች ላይና አንዴ በመሰንነው ጉዳይ ግትርነትን ማሳየት (Rigidity)÷
- የልጆችን ባህርይ ሌላ ሰው (ዘመድ፤ ጓደኛ፤ ህብረተሰብ፤ ቲቪ፤ ኢንተርኔት) እንዲቀርፀው መፍቀድ÷

- ልጆችን የመገናኛ ነጥብ ሳይሆን የመለያያ ምክንያት (Point of Departure) አድርጎ መውሰድ፡
- ልጆችን ከእግዚአብሔር ይልቅ የበለጠ መውደድ (1ሳሙ 2:29 ፤ 1ሳሙ 8:1 ፤ ማቴ 14: 1-12)፡
- የትዳር ዓለም ጣዕምና ክብር በሕይወት ከመኖር ይልቅ፤ በልጆች ላይ አለ ፡ታዊ ተፅዕኖ ማስተላለፍና ትውልዳቸውንም በክርስቶስ ቀጣይነት እንዲይ ኖረው ማድረግ (ምሳሌ፡ ከትዳር ውጭ በገሙት መውደቅ መፋታት፡ አንዱ ለሌላው አክብሮት በሚያሳጣ ሸካራና አስጨናቂ ባህርይ መኖር፡ ወዘተ)

2. ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ሊኖራቸው የሚገባ ግንኙነት፡

- ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆኑ መረዳት (መዝሙር 127: 3)፤
- ከእግዚአብሔር ቀጥሎ፤ ከአገልግሎት / ከሥራ ሩጫ ይልቅ ለቤተሰብ ልዩ ትኩረት በመስጠት ያልተቻኮለ ጊዜ ለልጆች መስጠት፤
- እግዚአብሔር ከእያንዳንዱ ልጅ ጋር የተለየ ዓላማ እንዳለው በማመንና በማሰብ የተለየ የፀሎት ጊዜ መውሰድ (1ሳሙ 1:1 ፤ 3:19-21 ፤ ሉቃስ 1:1-25 2ጢሞ 1:5)፤
- ለሚጠይቁን ትንሽም ይሁን ትልቅ ጥያቄ እውነተኝነት (Honesty) በሞላ በት ሁኔታ ባልተቻኮለ መንፈስ መመለስ፤
- ልጆች ጥፋት ሲያጠፉ በየዋህነት፡ በትዕግስት፡ በፅናትና በፍቅር ማስተካ ከል፡ መቅረፅና ማሳደግ፤
- እኛም ስናጠፋ ባጠፋነው ነገር ልጆቻችንን ይቅርታ መጠየቅ፤
- ለትውልዳችን ሁሉ የሚተላለፍ የእግዚአብሔር ክብር የሞላበት የፅድቅና የቅድስና ኑሮ በልጆቻችን ፊት መኖር።

3. ለወላጆች የሚሆን የዲሲፕሊን መመሪያዎች፥

- ወላጆች ልጆቻቸውን ዲሲፕሊን ለማድረግ የሚጠቀሙበት መንገድ የሚ ሠራ እንዲሆን ከተፈለገ በየጊዜው ተለዋዋጭ ያልሆነ (Consistent) መሆ ን አለበት። ልጆች የትኛው ትክክል ፤ የትኛው ደግሞ ጥፋት ያለበት ባህ ርይ እንደሆነ ከመጀመሪያው ሊነገራቸው ያስፈልጋል። ወላጆች ልጆቻ ቸው ጥፋት በሚያጠፉበት ጊዜ ለጥፋታቸው የሚሰጣቸው ዲሲፕሊን ካጠፉት ጥፋት ጋር የሚመጣጠንና ደግሞ የታወቀና ግልፅ የሆነ (predictable) እንደሚሆን መግለፅ ይኖርባቸዋል።

- ወላጆች የሚጠቀሙበት የዲሲፕሊን መንገድ የልጆቻቸውን ዕድሜ ግም ት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል። (ሉቃስ 2:51-52) ቁንጥጫ ወይም ሌላ በፍቅርና በዓላማ የሚደረግ ቅጣት (Physical discipline) አሥር ዓመት በላይ ዕድሜ ላላቸው ልጆች አይሰራም። ከአሥር ዓመት በላይ ላሉት ልጆች የሚሠራው የግል ኮንፈረንስ (Personal Conference/ one-to-one conference)፤ በአዕምሮ ሚዛን ማውጠንጠን (Reasoning)፤ ምክክ ር (dialogue)፤ ወይንም ይህን የሚመስል ነው።

- የዲሲፕሊን አሰጣጣችን የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት ያደረገ ፤ ያልተ ዛባ ሚዛንና (Fairness) ፤ ፍትህ የሞላበት (Justice) ሊሆን ይገባዋል። የዲ ሲፕሊን መጠኑ ልጆቹ ካጠፉት ጥፋት የሚመጣጠን ሊሆን ይገባዋል እን ጂ ፥ "የወላጅነታችን ክብር" ስለተነካና ፥ በውስጣችን ያለውን ትዕቢት ስለተነካ ለዚያ አጠፊታ መመለሻ ሊሆን አይገባውም። በአንፃሩም ልጆች ላጠፉት ጥፋት ወላጆች በቸልታና ወይም በግዴለሽነት ከተመለከቱት ለልጆቹ በጣም አደገኛ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያመጣ መልዕክት የሚያስተ ላልፍ ይሆናል። ያልተዛባ ሚዛን ያለው መንገድ መጠቀም (Fairness) የወላጅን ድምፅ ብቻ የሚያስተጋባ ሳይሆን፤ ልጆቹም ስለሁኔታው ያላቸ ውን የግል አመለካካት እንዲገልፁ፥ እንዲያስረዱና ወላጆችም እንዲረዱ

ቸው ባልተጭበረበረ አዕምሮ (Unbiased mind) ማዳመጥም ያካትታል። አለበለዚያ ግን ሚዛን ባለው መንገድና ፍትህ በተሞላ ሁኔታ ልጆች ከወላጆቻቸው የሚመጣውን ዲሲፕሊን ለመቀበልም ከመቸገራቸውም በላይ ካደጉም በኋላ በውስጥ መራራነትን ሊያሳድጉና በወላጆቻቸውም ላይ የመበቀል አጠፌታውን ለመመለስ እንዲያቅዱ ያስገድዳቸዋል። (ቆላ 3:21 ፤ ኤፌ 6:1-4)

- የዲሲፕሊን አሰጣጥችን ልጆቻችን በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራቸውንና የእያንዳንዱን ልጅ ልዩ ስብዕና (Unique Personality) በማስተዋል ፤ በመረዳትና ግምት ውስጥ በማስገባት ሊደረግ ይገባዋል። የዲስፕሊን ዋና ዓላማ ልጆቻችን ከስህተት ለመጠበቅ ፤ ካሉበትም ሁኔታ ለማውጣትና ወደፊትም በተመሳሳይ ስህተት እንዳይወድቁ ለማድረግ ነው። በአንዳንዱም በክርስቶስ ውስጥ እንዳሉ ሰዎች ባህርያቸውን ለመቅረፅ ፤ በእግዚአብሔር ፍርሃት እንዲያድጉ ለማድረግና ለራሳቸው ፤ ወደፊት ለሚሰሩት ቤተሰብ ፤ ለህብረተሰቡና በረከት የሚሆኑ ትውልዶች እንዲሆኑ ለማድረግ ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ ከፀሎት ድጋፍ ጋርና ለወደፊት ዘመናቸውም ራዕይ ባለው የፀና አላማ የሚደረግ ነው። ወላጆች ምንም ግዜ ቢሆን ማሰብ ያለባቸው ለአንዱ ልጅ የተጠቀሙበት የዲሲፕሊን አሰጣጥ መንገድ ለሌላው ልጅ ሊሠራ አለመቻሉን ነው። እያንዳንዱ ልጅ አፈጣጠሩም ሆነ ባህርዩ ልዩ ልዩ የሆነውን ያህል፥ የዲሲፕሊን መንገዱም እንዲሁ ልዩ ልዩ ሊሆን ይችላል፥ ይገባዋልም።

- ዲሲፕሊን በፍቅርና በትዕግስት፥ በተገዛና በተሰበሰበ መንፈስ ውስጥ ሆነን ሊደረግ ይገባዋል እንጂ፤ በቁጣ ፥ በንዴት ፥ ወይንም በጩኸት ሊደረግ አይገባውም። ወላጆች የልጆቻቸው አለመታዘዝ የግላቸው (personalize) አድርገው ከመውሰድ ሊቆጠቡ ይገባል። ይልቁንም የልጆቻቸውን ዕድገት በልባቸው ውስጥ ዋና ነገር አድርገው በመውሰድና የልጆቻቸውን በጎነት በማሰብ ሊያደርጉት ይገባዋል።

- ዲሲፕሊን የልጆችን የወደፊት ዕድገት (Development)÷ የወደፊት ተስፋ ና (Hope)÷የወደፊት ዓላማ (Goal/Purpose) ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባዋል፡ ፡ በምሳሌ 22፡6 ላይ "ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለ ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።" እንዳለው የወደፊት ዘመናቸውን በማሰብ ሊደ ረግ ይገባዋል። ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይ መስልም። ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈ ራላቸዋል።" (ዕብ 12፡11)

- ዲሲፕሊን ለማድረግ ያህል ብቻ የሚፈፀም ሳይሆን (በራሱ ፍጻሜ የለው ምና) የወላጆችና የልጆች የግኑኝነት ሥምረት የሚያጠናክር ÷ ውበትን የሚጨምር ዘላቂነት ያለው የወላጅና የልጅ "ጓደኝነት" (friendship) የሚፈጠር ሊሆን ያስፈልጋል። ዲሲፕሊን የግኑኝነት ሥምረት ካልፈጠረ ግን ጊዜአዊ የሆነ የባህርይ ለውጥ ሊያመጣ ቢችልም ፡ እየዋለ እያደር ግን በልጆችም ሆነ በወላጆች ውስጥ መራራነት (bitterness) የሚያስከትል ሊሆን ይችላል። ልጆቻችን ሳይንቲስቶች በላቦራቶሪ ውስጥ አስገብተው ለተለያየ ምርምር (research) እንደሚጠቀሙባቸው አይጦችና ለተወሰነ ነገር የሚያሳዩት የባህርይ ሽግግር ለምርመራ እንደሚጠቀሙባቸው እንስ ሶች ሳይሆኑ፡ በእግዚአብሔር አምሳል በዓላማ የተፈጠሩና ልዩ ስብዕና ያላቸው የከበሩ ሰዎች ናቸው።

ለግልና ለቡድን ውይይት የሚረዱ ጥያቄዎች÷

1. ክርስትያን ወላጆች ልጆቻቸውን እንዴት ሊያሳድጉ ይገባቸዋል ትላለህ?

2. ስለ ብቸኛ/ ነጠላ ወላጆች የተጠቀሱት ሐሳቦች ምንድናቸው?

3. ልጆችን የማረም/ የመቅጣት/ ዲሲፕሊን የማድረግ ጉዳይ በተመለከተ በውጭው ዓለም ያለው አስተሳሰብ ምን ይመስልሃል?

4. ወላጆች ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ የሚጠቀሙባቸው አፍራሽ ተፅዕኖ ያላቸው መንገዶች ምን ምንድናቸው?

5. በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የወላጆችና የልጆች ግንኙነት እንዴት ሊሆን ይገባል ትላለህ?

6. ወላጆች ልጆቻቸውን ዲሲፕሊን ለማድረግ ሲፈልጉ ትልቅ ግምት ሰጥተው ሊያስቡባቸው የሚገቡ ነገሮች ዘርዝር::

7. ከዚህ ምዕራፍ በግልህም ሆነ እንደወላጆች ልታስቡባቸው የሚገቡ መመሪያዎች? ማሳሰቢያዎች? ማስጠንቀቂያዎች? ልትወስዱአቸው የሚገቡ እርምጃዎች ምንድናቸው?

ምዕራፍ አሥር

በጋብቻና በቤተሰብ ላይ የሚነሱ ተግዳሮቶች

ሀ. በጋብቻና በቤተሰብ ላይ የሚመጣ መንፈሳዊ ውጊያ+

ጋብቻና ቤተሰብ በዓለማት ላይ ካለው መንፈሳዊ ውጊያና ከሰይጣንም ጥቃት ነጻ ሊሆን አይችልም። በአንድ በኩል እግዚአብሔር በፈጣሪነት ችሎ ታውና ዓላማው ጋብቻንና ቤተሰብን መመስረቱ ፣ መንከባከቡና መምራቱን ስናይ ፣ በሌላ በኩል ሰይጣን ደግሞ ይህንን የእግዚአብሔርን አላማ ለማፍረስ ያልተቋረጠ ውጊያ ማካሄዱ በልምምድ እውቀት (experientiaļ Knowledge) የምናየው ጉዳይ ነው። ሰይጣን የሚያመጣውን ውጊያ በተመለከተ በርካታ መጻህፍት ተፅፈው እናገኛለን።[69] ሆኖም በቤተሰብና በጋብቻ ላይ ያተኩሩ ግን ከጥቂት መጻህፍት በስተቀር ብዙ የሉም።[70] በጋብቻና በቤተሰብ ላይ የተ

---

[69] Clinton E. Arnold, *Three Crucial Questions About Spiritual Warfare*, (GrandRapids,Michigan: Bokg, 1997); Arnold, *Power of Darkness : Principalities and Powers in Paul's Letter*, (Leincerter, Downers Grove, Ill : Inter Varsity Press, 1992); Sydney H. T. Page, *Power of Evil : A Biblical Study of Satan And Demons*, (Grand Rapids, Michigan: Baker 1995); David Beck , "Spiritual Warefare," in Michael J. Anthony, ed., *Evangelical Dictionary of Christian Education*, (Grand Rapids, Michigan: Baker, 2001): 660-662.

[70] ለምሳሌ÷ Evelyn Christenson, *What Happens When we Pray for our Families*, (Colorado Springs, CO: Chariot, 1992).

ጻፉትን አብዛኛዎቸን መጻህፍትና መጣጥፎች ስንመለከት፣ መንፈሳዊ ውጊያ ከጋብቻና ከቤተሰብ ጋር የተያያዘ አነጋጋሪ ጉዳይ አድርገው አይወስዱትም፡ ፡ እንደ እግዚአብሔር ሰዎች ግን በጋብቻና በቤተሰብ ላይ የሚነሳ የእግዚአ ብሔርም ሆነ የቅዱሳን ጠላት ሰይጣን እንዳለና የሚያስነሳውም መንፈሳዊ ውጊያ (Spiritual Warfare) እንዳለ መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው።

ከፍጥረት በኋላ ብዙም ሳይቆይ መንፈሳዊ ውጊያ ከቤተሰብ ህይወት ጋር የተያያዘ ጉዳይ እንደሆነና፣ በአሪትዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ላይ ሰይጣን በእ ባብ ተመስሎ አዳምና ሔዋንን ኃጢአት እንዲሰሩና የስህተትም አሰራር ውስ ጥ(Deception) ሲያስገባቸው እንመለከታለን። ሰይጣን በአዳምና በሔዋን ፊት ያቀረበውም ፈተና እግዚአብሔር እንደማያስፈልጋቸውና የራሳቸውም አም ላክ መሆን እንደሚችሉ በመጀመሪያ ሔዋንን ፡ ከዚያም አዳምን ሲያስታቸ ው እንመለከታለን። በዚህም ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ከመግባቱም በላ ይ፣ እግዚአብሔር የሰው ልጅ በኃጢአት ሰበብ ሥጋዊ ሞት ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ሞትም እንደሚሞት ሲናገረው እናያለን።

ሰይጣን በቤተሰብ ላይ ካመጣው መንፈሳዊ ውጊያ በአሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ላይ የግለሰብ ኃጢአት ስናይ፣ በምዕራፍ 4 ግን መልኩን ለውጦ የቤተሰብ ኃጢአት ሲሆንና ቃየን ወንድሙን አቤልን በቅንዓትና በአመጽ ሲገ ድለው እንመለከታለን። በዚህ ብቻ አላቆመም ፡ ከግለሰብ ወደ ቤተሰብ የተዛ መተው ኃጢአት፣ ከምዕራፍ 5-11 እንደምናየው ወደ ህብረተሰብ ሲዛመትና ህብረተሰቡም መበስበስ ውስጥ በመግባቱ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ሲፀፀት (6:5-6) ስንመለከት፣ የሰይጣን ውጊያ በቤተሰብ ላይ ምን ያህል መዘ ዝ እንዳመጣ እንገነዘባለን።[71]

---

[71] Andreas J. Kostenberger, "Marriage and Family in the New Testament." in Ken M. Campbell, ed., *Marriage and Family in the Biblical World*, (Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2003): 207.

አዲስ ኪዳንም መንፈሳዊ ውጊያን በተመለከተ የተለየ አስተሳሰብ የለ ውም:: ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 6:10-20 ድረስ የገለፀው መንፈሳዊ ውጊያ የቤተሰብን ጉዳይ (5:21-33) በሰፊው ከተነተነና የወላጆችንና የልጆች ን ግንኙነትን ከገለፀ በኋላ (ኤፌሶን 6:1-4) መሆኑ የሚያስደንቅ አይደለም:: ሐዋርያው ጳውሎስ የቤተሰብ ግኑኝነት ሥምረት ለማቋረጥ ወይም ለማጨናገ ፍ መንፈሳዊ ውጊያ እንዳለና የዚህም ውጊያ ጠንሳሽ የሆነው ሰይጣን እንዳለ መገንዘቡን ኤፌሶን 6:10-20 ላይ ያለው ሃሳብ አስፈላጊነት የበለጠ ያጠነክረ ዋል::[72]

የኤፌሶን መጽሐፍ በተመለከተ ብዙ የተለያዩ ጸሐፊዎች በልዩ ልዩ መግለጫ ገልፀውታል:: ከእነዚህም መካከል ዎች ማን ኒ (Watch Man Nee) የተለባው የቻይና ተወላጅ ጸሐፊ "ተቀመጥ" (ምዕራፍ 1-2)÷ "ተራመድ" (ምዕራፍ 3÷1-6÷4) እና "ቁም" (ምዕራፍ 6:10-20) ("Sit, Walk, Stand") በሚል መግለጫ በመስጠት ጥሩ መፅሐፍ ፅፏል::[73]

ከዚህ የተሻለ ግን የኤፌሶንን መጽሐፍ በሚከተሉት ርዕሶች አከፋፍሎ ማጥናት ይቻላል::

- በክርስቶስ ያለውን አዲስ ሕብረተሰብ (ምዕራፍ 1:3-2:10)
- የአዲሱ ሕብረተሰብ ገፅታ (ምዕራፍ 2:11-3:21)
- የአዲሱ ሕብረተሰብ የኑሮ ዘይቤ (ምዕራፍ 4:1-5:20)
- የአዲሱ ሕብረተሰብ ግንኙነት (ምዕራፍ 5:21-6:24)[74]

---

[72]Peter T. O'Brien, *The letter to the Ephesians, Pillar New Testament Commentary*, (Grand Rapids , Michigan : Eerdmans 1999), 457.
[73]Watch Man Nee, *Sit, Walk, Stand*, (Wheaton, ILL.: Tydale House, 1977).
[74]በኤፌሶን መጽሐፍ ላይ የጠለቀ ጥናት ለማድረግ+ John R. W. Stott, *The Message of Ephesians: God's New Society* in *The Bible Speaks Today Series*, (Downers Grove, ILL.: InterVarsity Press, 1986) ይመልከቱ::

ሐዋርያው ጳውሎስ የቤተሰብን ግንኙነት (በባልና ሚስት መካከልና በወላጆችና በልጆች መካከል) ከመጥቀሱም በፊት፥ በትዳር መሃል የአልጋ ንፅህና (Sexual Purity) (ምዕራፍ 5:3-7)፤ በብርሃን መመላለስ (ምዕራፍ 5:8-14)፤ እና ጥበብ እንደሚያስፈልግ ከገለፀ በኋላ ነው። በእንዲህ ዓይነት ንፅህና (Purity) ቅድስና (Holiness) ባለው የቤተሰብ ህይወትና ኑሮ በብርሃንና በጥበብ ለመመላለስ ግን ፥ "መንፈስ ይሙላባችሁ" (ምዕራፍ 5:18) እንዳለው በመንፈስ ቅዱስ መሞላት (በመንፈሳዊ ህይወት ለመታነፅና ለማደግ) እና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሞላት (Filling of the Holy Spirit and Empowerment of the Holy Spirit) ሌሎችን የቤተሰብ አካላትም ይሁን የውጭውን ህብረተሰብ በንፅህናና በቅድስና ለማገልገል በጣም ወሳኝ ነው። (የሐዋ ሥራ 1:8 ፤ 2:1-4)[75]

ስለዚህ በኤፌሶን 6፥ 10-20 የተገለፀው መንፈሳዊ ውጊያ በምዕራፍ 5፥ 18 የተገለፀውን ሐሳብ በማጠናከር "*የመንፈስን ሰይፍ ያዙ*" በሚ ል ቃል ይቀጥለዋል (ምዕራፍ 6:17)። እንዲያውም ይህ መንፈሳዊ ውጊያ በመሆኑ ፥ "*መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ሰፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ ::*" (6:11-12) በተጨማሪም ሐዋርያው ጳውሎስ በ2 ቆሮንቶስ 10:3-6 ላይ እንዲህ ይላል ፥ "*በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን ፥ እንደሰው ልማድ አንዋጋም ፤ የጦር ኢቃችን ሥጋዊ አይደምና*፤"[76] ስለዚህም የቤተሰብ ጉዳይና መንፈሳዊ ውጊያ በቅር

---

[75]ለሰፊ ሙይይት የሚከተለውን ማንበብ ይቻላል፥ Andreas J. Kostenberger, "What Does It Mean to be Filled With the Spirit? A Biblical Investigation," *Journal for the Evangelical Theological Society* 40 (1997): 229-240.

[76]የሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 6: 10-20 ያለውን ሐሳብ ትንታኔ ለማጥናት የሚከተለውን ማንበብ ይቻላል፥ Peter T. O'Brien, *Gospel and Mission in the Writings of Paul: An Exegetical and Theological Analysis*, (Grand Rapids Michigan: Baker, 1995), 109-131; Andreas J. Kostenberger and Peter T. O' Brien, *Salvation to the Ends of the Earth: A Biblical Theology of Mission – New Studies in Biblical Theology*, (Downers Grove, ILL: InterVarsity Press, 2001), 196-198.

በት ማውጠንጠናችን የጌታ ቃል በግልፅ ከማሳየቱም በላይ፤ በልምምድ ስና የው አግባብ ያለው አመለካከት ነው።

1. አዕምሮን ለመያዝ የሚደረግ ጦርነት/ ውጊያ÷ (Battle for the Mind)

በመንፈስ የውጊያ ዓለም ውስጥ ማወቅ ያለብን ነገር ትልቁ ውጊያው የሚጀምረው አዕምሮ ውስጥ መሆኑንነው። ሰይጣን ቤተሰብን ለመዋጋት÷ ቢቻለውም ለማፍረስ የሚጠቀመው የእያንዳንዱን ሰው ቀልብ (rational mind) ለማጨለም በመሞከር ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላል÷ "*ነገር ግን እባብ በተንኮል ሔዋንን እንዳሳታት÷ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንፅህና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ*።" (2ቆሮ 11:3 ፤ 10:3-6 ፤ 1ዮሐ 2:15-16) እንዲህ ዓይነት የአዕምሮ ውጊያ ሰይጣን በቤተሰብ ላይ በሚያመጣበት ጊዜ ÷ የጠላትን አሠራር ባለመ ሳትና ባለማሳነስ ÷ የጠላትን ማንነትም ለይቶ በማወቅ÷ በውጊያ ጊዜ የሚጠ ቀሙበት የመሣሪያ አይነት (ኤፌ 6:10-20) እና የውጊያውንም ዓላማ መወሰ ን በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚህም በማያያዝ የቅዱሳን ጠላት የሆነው ሰይጣን በቤተሰብ ላይ ከሚያመጣቸው ፈተናዎች (temptations) መካከል ጥቂቶቹን እንመለከታለን።

2. የሰይጣን መፈተኛ መሣሪያዎች÷

- **የዝሙት ፈተና (SexualTemptation)÷**
- **ቁጣ (Anger)÷ እና**
- **ስሜት የለሽ/ ግድየለሽ መሆን (Insensitivity/ Indifference) ÷**

(ሀ) አንደኛ÷ ከሰይጣን መሣሪያዎች አንዱ የዝሙት ፈተና (Sexual Temptation) ከመሆኑም ሌላ፣ ብዙ ባለትዳሮችም የኃጢአት ወጥመድ ውስጥ እንዲገባ ያደረገና በመጨረሻም ትዳራቸውን ለመፍረሱ ምክንያት የሆነ ጉዳይ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ 1ቆሮ 7:5 ላይ ÷ "*ለፀሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ ፤ ራሳችሁን ስለአለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ።*" ይላል። ይህ የሚያመለክተው በባልና በሚስት መካከል የሚደረገውን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት (Sexual Intimacy) ማጥቃት የሰይጣን አንዱ ዒላማው እንደሆነ ነው።

(ለ) ሁለተኛው÷ የሰይጣን መሣሪያ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ቁጣና (uncontrolled anger)÷ መፍትሔ ያልተገኘለት ቁጣ (unresolved anger) በቤተሰብ አባላት መካከል ከፍተኛ ጉዳትን ÷ ድንጋጤንና ÷ ምናልባትም ሞራትን የሚያመጣ ጉዳይ ነው። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 4:26-27 ላይ "ተቆጡ ኃጢያትንም አታድርጉ ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ ÷ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።" ያለው። በተጨማሪም በአባቶች ላይ በማተኮር÷ "*አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣፅ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጡአቸው።*" ይላል።(ኤፌ 6:4 ÷ ቆላ 3:21)

(ሐ) ሦስተኛው÷ የሰይጣን ውጊያ መሣሪያ በተለይም በባሎችና በሚስቶች መካከል በሚነሣው ግጭት የተነሳ ስሜት የለሽ/ ግድየለሽ መሆን ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላል ÷ "*ባሎች ሆይ ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ መራራም አትሁኑባቸው።*" (ቆላ 3:19) ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደዚህ ይላል÷ "*እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ÷ ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ፀሎታችሁም እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ፀጋ እንዲወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው።*" (1ጴጥ 3:7)

ይህንን ሐሳብ ለማጠቃለል ሰይጣን በቤተሰብ መካከል የሻከረ መንፈስ ለማምጣት ÷ የግንኙነት ስምረትን ለማበላሸት ÷ ግንኙነትንም ለመስበር ÷ በመጨረሻም ከሆነለት ባለመግባባት የተጀመረውን ችግር ትዳርን ያህል ነገ ር ለማፍረስ የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች የዝሙት ፈተና ÷ የቁጣ መንፈስ ና ስሜት የለሽነትና ግድየለሽነት (Indifference/ Insensitivity/ Inconsiderate) በመሆናቸው በትዳር ዓለም ያሉ ክርስቲያን ቤተሰቦች ሊያስ ተውሉና መንፈሳዊውን ውጊያ በድል እንዲወጡ ያስፈልጋቸዋል::

3. መንፈሳዊ ውጊያን በድል ለመዋጋት የሚያስችል መፍትሔ÷

መንፈሳዊ ውጊያ ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ የነበረና አሁንም ያለ ቤተሰባ ዊ እና እንደ እግዚአብሔር ሰዎች እንደሚገባ መዋጋት ብቻ ሳይሆን ውጊያ ውን በድል እንዴት ልንደመድመው እንደምንችል የእግዚአብሔር ቃልስ ስለ ዚህ ምን እንደሚልና ሦስት ቁልፍ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለመመልከት እንሞ ክራለን::

(ሀ) በመጀመሪያ መንፈሳዊ ውጊያ እንዳለ ማወቅ ወሳኝ ነው:: በቤተሰብ ላይ መንፈሳዊ ውጊያ እንዳለ አለማወቅ ÷ እያወቁ ቸል ማለት ÷ ወይንም ፊፅሞ በእኛ ላይ ሊመጣ እንደማይችል አድርጎ መቁጠርና÷ እንደሌለም መካድ (denial) ለፈተናው እንድንጋለጥ ያደርገናል:: በዘመናችን አማኝ በሆኑ ቤተሰቦችም ሆነ አማኝ ባልሆኑ ቤተሰቦች መሃል ፍቺ ከመጠን በላ ይ እየበዛ መምጣቱ ባለትዳሮች ትዳራቸውን ለመያዝ ስላልፈለጉ ÷ እው ቀቱ ሊሰጣቸው የሚችል ትምህርት በማጣት÷ ወይም የፍቅር ማጣት ጉዳ ይ ሳይሆን፤ ብዙዎች መንፈሳዊ ውጊያ እንዳለ አውቀው ራሳቸውን ከሰ ይጣን ወጥመድና አሽክላ መጠበቅ ስለተሳናቸው ነው::

(ለ) ሁለተኛው ደግሞ የእኛ ጠላት ሰው ሳይሆን (ባል የሚስት ጠላት/ ሚስት ም የባል ጠላት ሳይሆኑ) ከማንም ሰው የግንኙነት መበላሸት በስተርጀባ

አውራ ጠላት የሆነውና በቅዱሳንም ላይ ጦርነትን የሚያመጣው ሰይጣን እንዳለ ሳወቅ ይኖርብናል። ይህ ጠላት እኛን ለማሳት የተለያዩ መንገዶችን ፥ ዘዴዎችንና፥ ልዩ ልዩ ገፅታ ያላቸውን ዘይቤዎችን ይጠቀማል። (2ቆሮ 10:4 ፥ ኤፌ 6:11 ፥ 1ጴጥ 5:8-9) ሰይጣን ምንም እንኳን በመጀመርያ የመላዕክት አለቃ የነበረ የጠለቀ እውቀት የነበረውና አሁንም ያለው ቢሆንም፥ የወደቀ መልአክ ነው። አምላካችን እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ (Omniscient)፥ በሁሉ ሥፍራ የሚገኝ (Omnipresent) እና ሁሉን የሚችል (Omnipotent) እንደሆነ እናምናለን፥ እናውቃለንም። ሰይጣን ግን የተጭበረበረና ውሱን እውቀት ያለው፥ በቦታና በሥፍራ ውሱን፥ በችሎታው እግዚአብሔር ካልፈቀደለት በስተቀር አቅምና ጉልበት የሌለው ፍጡር ነው።

(ሐ) መንፈሳዊ ውጊያ መፅሐፍ ቅዱሳዊ በሆኑ አግባብ ያላቸው መሣሪያዎች በመጠቀም ልንዋጋ ይገባል። አንዳንድ ቤተሰቦች ውጊያው እየናረና እየጠለቀ ሲመጣ፥ ይህንን የሰይጣን አሰራር በፅናት መቋቋም እንዳለባቸው ሳይገነዘቡ ይቀሩና በመደናገጥ ውጊያውን ጥለው የመሰላቸውንና ያዋጣል ያሉትን አማራጭ መንገድ ይወስዱና በጠላትእጅ ይወድቃሉ። ሌሎች ደግሞ ምንም እንኳን በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ እንዳሉ ቢያውቁም ትክክለኛና አግባብ ያለውን መሣርያ ባለመጠቀማቸው በውጊያው መሣል ይሸነፋሉ። ስለዚህም <u>በኤፌሶን</u> 6:<u>10-18 የተገለፁትን የመንፈሳዊ ውጊያ መሣሪያዎች</u> በዝርዝር ማየቱ አስፈላጊ ነው።

- "<u>*እንግዲህ መግባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ*</u>"፥ ባልም ሆነ ሚስት እርስ በእርሳቸው በሚነጋገሩአቸው ጉዳዮች ሁሉ "ውሸትና መለባበጥን" አስወግደው እውነትን ሊነጋገሩ ይገባል። (ኤፌ. 4:25) በአንፃሩ "*እውነትን በፍቅር*" እየያዙ "*ባነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ*" ሊያድጉ ያስፈልጋቸዋል። (ኤፌ. 4:15) በተጨማሪም ፥ "*ለሚሰሙት ፀጋን ይሰጥ ዘንድ እንደሚያስፈልግ ለማነፅ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል*

እንጂ ክፉ ቃል ከአፋቸው እንዳይወጣ ሙሉ ጥንቃቄ ሊመስዱ ይገባል። (ኤፌ. 4:29)

- "*<u>የፅድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ</u>*"÷ ፅድቅ በአንድ መልኩ በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ በኩል ትክክል (up-right) ሆኖ መቆምን ሲያመለክት (ሮሜ 5:1-9 ÷ 2ቆሮ. 5:12) ፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ከእግዚአብሔርና ከወንድም/ከእህት ጋር ያለንን የፍቅር ግንኙነት ያመለክታል። <u>ምክንያቱም የአባትን ጉልበት ስሞ ÷ የወንድምን/የእህትን ጉንጭ መንከስ አይቻልም!! ሙሽራ ሆኖ የሚመጣውን ጌታን ወዶና÷ ሙሽራይቱን/የክርስቶስን አካል/ቤተ ክርስቲያንን መናቅ ወይንም መጥላት አይቻልም።</u> (መዝ 15: 1-5÷ ማር. 12:29-31)

- "*በሰላም ወንጌል በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ*"÷ ክርስትያን ቤተሰቦች መረዳት ያለባቸው ነገር ጌታን ከተቀበሉበት ዘመን ጀምሮ በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት በውስጣቸው ልዩ ሰላም ያላቸው መሆኑን ብቻ ሳይሆን፤ ይህ አምነው የተቀበሉት ጌታ÷ "የሠላም አለቃ" (Prince of Peace) መሆኑንም ጭምር ነው። (ኢሳ. 9:6÷ ዮሐ. 14:27 ÷ 16:33÷ 1:12÷ 1ዮሐ 3:1÷ ሮሜ 5:1÷ ማቴ 5:9÷ 2ቆሮ 5: 17-18)÷ : <u>**የብሉይ ኪዳን ሰላም/ ሻሎም (Shalom) ከእግዚአብሔር ÷ እርስ በእርስ ÷ ከራስና ከአካባቢ ጋር ሁሉ የሚያጠቃልል የነበረ የጠለቀ እሳቤ (Concept)** ነው።</u> የእያንዳንዱ ክርስትያን ምልክት (mark of a Christian) "ሰላም" መሆን ያለውን ያህል÷ በባልና ሚስት መሃልም ይሁን÷ በወላጆችና በልጆችም መካከል÷ እንደ ክርስቲያን ቤተሰቦች ሰላምን ልንዘራና የሰላም ሰዎች ልንሆን÷ በዓለም ያሉት አማኝ ያልሆኑ ሰዎች አይተው በውስጣችን ካለው "የሰላም አለቃ" (Prince of Peace) ከሆነው ጌታ ጋር ሊታረቁ የሚያስችል÷ የሚያጓጓና÷ የሚጋብዝ ሕይወት ሊኖሩ ይገባል።

- "*<u>የእምነትን ጋሻ አንሡ</u>*"÷ ክርስቲያን ቤተሰቦች የጌታ ደቀመዛሙርት በመሆን ጌታ ራሱ "*ሀይወቱን ሊያገኝ የሚወድ ያጠፋታል ፤ ሀይወቱን ግን ስለእኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።*" እንዳለው ሀይወታቸውና ኑሮአቸውን ለጌታ አደራ በመስጠት ፥ ሐዋርያው ጳውሎስም ፥ "*ያመንሁትን አው ቃለሁና፥ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ።*" (2ጢሞ. 1:12) እንዳለው በእምነት ሊመላለሱ ፤ ጳውሎ ስ በሌላም ስፍራ ÷ "*እንግዲህ ታምነን÷ በእምነት እንጂ በማየት አንመላ ለስምና*፥"(2ቆሮ. 5:6) እንዳለው ለሚያስፈልጋቸው ጉዳይ ÷ በሚያጋጥማ ቸው ቀውጢ ሁኔታዎች (Challenges)÷ እና ፊት ለፊትም በሚጋፈጡት መንፈሳዊ ውጊያ መሣል እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታና በአሸናፊነት እንደሚመራቸውና እንደሚያወጣቸው በእምነት ሊቆሙ ያስፈልጋቸዋል፡ ፡ (ማቴ 6:25-34) ምክንያቱም "*እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ሁሉ - አዎን ማለት በእርሱ ነውና ፤ ስለዚህም ለእግዚአብሔር ስለ ክብሩ በእ ኛ የሚነገረው አሜን በእርሱ ደግሞ ነው።*" (2ቆሮ. 1:20) (NIV "For no matter how many promises God has made, they are "yes" in Christ. And so through Him the "Amen" is spoken by us to the glory of God.") ንጉሥ ዳዊትም በመዝሙር 145:14 ላይ እንዲህ ይላል። "*እግዚአ ብሔር በቃሉቹ የታመነ ነው፥ በሥራውም ሁሉ ፃድቅ ነው።*" (NIV. "The Lord is faithful to all His promises, and loving toward all He has made.")

- "*<u>የመዳንን ራስ ቁር</u>*"÷

ባልና ሚስት በክርስቶስ በኩል ያገኙትን የደህንነት ደስታ በየጊዜው ሊታደስና በእግዚአብሔር ፊት የምስጋና መስዋዕት ለማቅረብ ምክንያት ሊሆናቸው ይገባል። የመዳናቸው ደስታና ተስፋ በውስጣቸው በየጊዜው በሚታደስበት ጊዜ ለጠላት አሰራር ራሳቸውን አሳልፈው አይሰጡም። ምክንያቱም በመዳኑ በየዘመኑ ሐሴት የሚያደርግ ባል ሚስቱን የባልነት

ስልጣኑን አለአግባብ በመጠቀም የሚያስጨንቅ ሳይሆን ÷ የዘላለም እህቱ የሆነችውን ሚስቱን በፍቅርና በአክብሮት የሚይዛት ይሆናል። ሚስትም እንዲሁ ለባልዋ አክብሮት ለማሳጣትና "ሌላ ባል" ለመሆን ከመሞከር ይልቅ ያለማቋረምረምና የባልዋን አመራር በደስታ በመገዛት ጌታን የም ታስከብር ሴት ትሆናለች። (ኤፌ. 5:21-33)

- *"የመንፈስም ሰይፍ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው"÷*

የእምነታችን መሰረትና ለኑሮአችንም የህይወት መመሪያ የእግዚአብ ሔር ቃል በመሆኑ (ማቴ. 7:24-27÷ ዕብ. 4:12 ÷ 1ጴጥ. 1:23-25) ባልና ሚስት ራሳቸውን በየቀኑ በእግዚአብሔር ቃል ሥር አስቀምጠው በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በአድናቆትና በናፍቆት÷ በተከፈተ አዕምሮና በተሰጠ ልብ "*ሊሰሙት÷ ሊያነቡትና በውስጡም የተፃፈውን ሊታዘዙ*" ይገባቸዋል። (ራዕይ 1:3 ÷ ዮሐ. 8:31-32 ÷ 15:4-7) ባልና ሚስት በየ ግላቸው÷ በቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ÷ በሰንበት ትምህርት÷ በአሠ ድ አምልኮ ሊያጠኑት ይገባል። <u>ጥናት ማለት÷ "እውቀትን ለማግኘትና ለማቆየት ÷ ሥርዓት በያዘ መንገድ በዓላማ ÷ በተከፈተ አዕምሮና በተሰ ጠ ልብ በመንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት አዕምሮን መጠቀም ማለት ነው።"</u> (2ጢሞ 2:7 ÷ 4:2)

- *<u>"በፀሎትና በልመና ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ፀልዩ።"</u>*

ባልና ሚስት "*በሰላም ማሰሪያ የመንፈስ አንድነት ለመጠበቅ በመትጋ ት*" (ኤፌ 4:2-3) "*በነገር ሁሉ በፀሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚ አብሔር ዘንድ*" ልመናቸውን እያስታወቁ ÷ ከመጨነቅና ከመታወክ ይል ቅ በፀሎት ሊተጉ ይገባቸዋል። (ፊል. 4:5 ÷ 1ጴጥ. 5:7) አስፈላጊና ወሳ ኝ በሆኑ ወቅቶች የጠላት ውጊያ በበዛባቸው ጊዜያትና የእግዚአብሔርም ምሪት በተለየ መንገድ መጠየቅና መወሰን በሚኖሩባቸው ጉዳዮች በያምና

በፀሎት ራሳቸውን በጌታ ፊት በማቅረብና÷ ለዚህ ዓላማ ብቻ ከማብረ-ሥጋ ግኑኝነትም ለተወሰነ ጊዜ ሊቆጠቡ ይችላሉ:: (1ቆሮ 7:5)

ለ. ለቤተሰብ የሚሆኑ ማጠቃላያ ምክሮች÷

1. የቤተሰቡን ህይወት ለመጠበቅና እያንዳንዱ የቤተሰቡ አበላትም እግዚአ ብሔርን በማወቅ እየተሞላ በእግዚአብሔር ቤት እያደጉ እንዲመጡ ካስ ፈለገ እንደቤተሰብ አብረው የሚያመልኩበት ÷ የጌታን ቃል የሚያጠኑበ ትና የሚፀልዩበት ቢቻል በየቀኑ ፤ ካልሆነም በሳምንት ከሦስት ያላነሰ ጊዜያት ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ጊዜያት መደረግ ስላለበት የግዴታ÷ ሥርዓትን ለመጠበቅ ያህል (Legalistic)÷ በድርቅና (Rigidty) ÷ ወይንም በተቃራኒው በግድየለሽነት (Indifference) መደረግ የለባቸውም:: ይልቁንም ህይወት በሞላበት ሁኔታ በናፍቆት ÷ እንደልጆች እድሜ በየጊዜው መቀየር የሚችል ያልተንዛዛና የእያንዳንዱ ን የቤተሰብ አባል መንፈሳዊ እድገት ግምት የሚያስገባ ሊሆን ይገባዋል:: አባቶችም በቤተሰባቸው ካህን (ፓስተር/መጋቢ) እንደሆኑ አውቀው የቤተሰባቸውን መንፈሳዊ እድገት በመጠበቅ አመራራቸውን በሚገባ በቤ ተሰባቸው መሃል ሊገልፁ ይገባል:: አባቶች በቤተሰባቸው መሃል የሚያሳ ዩት የግል የህይወት ለውጥ ÷ የባህርይ ለውጥ ÷ መንፈሳዊ እድገትን መ ስጠት÷ ለእግዚአብሔር ቃልና ለመንፈስ ቅዱስ ያላቸው መሰጠትና መን ቀጥቀጥ÷ ለእግዚአብሔር ቤትም ያላቸው አክብሮትና ለቅዱሳን ያላቸ ው ፍቅር ለሚሰቶቻቸውም ሆነ ለልጆቻቸው መንፈሳዊ እድገት በጣም ወሳኝ ነው::[77] (ዘፍ 8:20-12 ፤ ኢያሱ 24: 15)

---

[77]ለሰፊ ውይይት የሚከተለውን ማንበብ ይቻላል÷ James W. Alexander, *Thoughts on Family Worship* (Morgan, PA: Soli Deo Gloria, 1998; Clay Clarkson, *Our Twenty-Four Family Ways: Family Devotional Guide* (Colorado Spring: Whole Heard—Press, 2004; Jim Gromarty, *A Book for Family Worship* (Harris Burg, PA: Evangelical Press, 1997); Terry L. Johnson, *The Family Worship Book : A ResourceBook for Family Devotions* (Fearn: Christian Focus Publications, 2000).

2. የቤተሰብ ግንኙነትን ለማጠናከር የቤተሰብ ባህላዊ ጊዜያቶች (Family Traditions) በየጊዜው መጠበቅና መንፈሳዊ ጣዕሙ በሚጠበቅ ሁኔታ እን ደቤተሰብ ማድረግ ነው። ለምሳሌ የልደትና የፋሲካ በዓላትን አብሮ ማሳ ለፍ፥ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት የምሥጋናን መስ ዋዕት ማቅረብ፥ ቤተክርስቲያን በሚኖረው የእሁድ አምልኮ ከተካፈልን በኋላ ቢቻል በእሁድ ምሽት እግዚአብሔር ምን እንዳስተማረን አብረን የምናሰላስልበትን አጭር ጊዜ መውሰድ፤[78]

3. "አብሮ የሚፀልይ ቤተሰብ አብሮ ይኖራል" የሚለው ታሳብ እውነት የሆነ ውን ያህል ፤ "አብሮ የሚፀልይና የሚጫወት ቤተሰብም አብሮ ይኖራል። " የሚለው አባባልም ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ልጆቻችን የቴሌ ቭዥን ወይም ኢንተርኔት ደንበኞች ሆነው እንዲያድጉ ለብቻቸው ከመ ተው ይልቅ ፡ ለእነዚህ የሚኖራቸውን ጊዜ በመወሰን አብዛኛውን ጊዜ ግን አብሮ ሳቅ በሞላበት ሁኔታ መጫወት መፃህፍትን ማንበብ ፡ ከቤት ውጪ የሆኑ ድርጊቶች (Oudtdoor activities) አብዝቶ ማድረግ፥ ከተለ መደው አካባቢ ወጥቶ ቢቻል በየዓመቱ ሱባዔ (Family Retreat) መውጣ ት፥ ታሪካዊ ቦታዎች (Historical Sites) መጎብኘት፥ በጣም አስፈላጊ ነገ ሮች ናቸው።

4. ከዚህ በፊት እንደገለፅኩት ሰይጣን በቤተሰብ ላይ የሚያመጣቸውን በየዘ መኑ መልካቸውን እየቀያየሩ የሚመጡትን መንፈሳዊ ውጊያዎችን እንደ ቤተሰብና እንደ አንድ ሰው ሆነን ፀንተን መዋጋት በጣም ወሳኝ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ "በእርሱ እንዳንታለል ፤ የሰይጣንን ታሳብ አንስተው ምና።" እንዳለው በነቃ አዕምሮና መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በእግ

---

[78]ስፋ ላለ ውይይት ተሚከተሉትን መመልከት ይቻላል፥ Gloria Gaither and Shirley Dobson, *Creating Family Traditions: Making memories in festive Seasons* (Sister OR : Multnomsh,2004); Noel Piper, *Treasuring God in our Traditions* (wheaton, Ill.:Crossway, 2003); Barbar Hughes, *Disciplines of a Godly Family* (Wheaton, Ill.:Crossway, 2004), 43-56.

ዚአብሔር ቃል ሥልጣን የሰይጣንን ፍላፃ ልንዋጋ ይገባል። የእግዚአብ ሔርን ቃል ልብ ብለን ስናጠና ቤተ ክርስቲያንን በድል እንደምታሸንፍ እንጂ፥ ተከላካይና ተሸናፊ አድርጎ ሲያስቀምጣት አናይም። (ማቴ. 16:1 3 19) በእንዲህ ዓይነት የድል ህይወት ለመኖር ካስፈለገ እያንዳንዱ ቤተ ሰብ በመካከሉ ያሉትን ችግሮች አለመግባባትና መበዳደል በትዕግሥት፥ በጥበብ፥ መደማመጥ በሞላበት ሁኔታ ከተነጋገሩ በኋላ እርስበርስ ይቅር በመባባልና አንዱ ሌላውን በምህረት በመቀበል የልባቸውና የትዳራቸውን ቋጠሮ ሊፈቱ ይገባል። በተጨማሪም እንደ እግዚአብሔር ሰዎች ችግሮ ቹ ሥር ከመስደዳቸው በፊት በመነጋገርና ይቅርታ በማድረግና በመቀባበ ል በወቅቱ ፡ ማለትም "በመካከላቸው ፀሐይ ሳይገባ" (ኤፌ. 4:25:32) ማለትም፥ ሳይውል ሳያድር ሊፈቷቸው ይገባል። ችግሮችና አለመግባባቶ ች በቤተሰብ መሃል እንዳይሰፍኑና እንዳይጠራቀሙ ከሚረዱት መንገዶ ች አንዱ በየሁለት ወይም በሦስት ወሩ አንድ ጊዜ እንደ ቤተሰብ በመሰባ ሰብ ፥ ፍፁም ነፃነትና ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ (Atmosphere) እያንዳን ዱ የቤተሰብ አባል ነፃ ሆኖ የሚናገርበት ራሳችንም ሆነ እርስ በርስ የም ንገመግምበት (Family business meeting) ማዘጋጀት በጣም ይረዳል። ይህ ጊዜ የፀሎት ወይም የእግዚአብሔርን ቃል የምናጠናበት ጊዜ ሳይሆ ን ያሉትን ችግሮች በግልፅ ተነጋግሮ መፍትሄ ለማግኘት ቤተሰብ የሚመ ካከርባቸው ጊዜያት ናቸው። በዚህ ጊዜም ይሁን በሌሎች የቤተሰብ ጊዜ አንዱ ለሌላው (ባል ለሚስት ፥ ሚስትም ለባል ፥ ወላጆች ለልጆች ፥ ልጆችም ለወላጆች) አክብሮት ሊገልፁና ራሳቸው የሚጠቅማቸውን ሳይ ሆን ሌላውን ለመጥቀም በማሰብ የሚያደርጉትን ሁሉ ሊያደርጉ ይገባል፡ : ከዚህም በላይ የእግዚአብሔር ክብር በቤተሰባቸው መሃል ያለመከልከል እንዲገለፅ በመናፈቅ ሊመላለሱ ይገባል። (ፊል 2:1-11)

ሐ. በትዳር ዓለም የሚከሰቱ ችግሮች÷

1. በትዳር ዘመናት በየደረጃው የሚያጋጥሙ ፈተናዎች÷

(ሀ) የመጀመሪያው ዓመት፡-

- የመጣጣም ወይም የመዋሃድ ችግር (Adjustment Problems)
- ትዳርን በዕዳ መጀመር::
- የቤተሰብና የንደኞች ጣልቃ ገብነት::
- እግዚአብሔር ከሰጠን ሰው ጋር ሳይሆን በአዕምሮ ከሳልነው ሰው ጋር መኖር:: (Ideal Person)

(ለ) የመጀመሪያዎቹ አምስት ዓመታት፡-

- ልጅ ባለመውለድ የሚመጡ ችግሮች::
- ልጅ ከመውለድ ጋር የሚመጡ ችግሮች::
    - ልጅን ዲሲፕሊን በማድረግ/ ባለማድረግ::
    - ልጅን የመጨቃጨቃችን ምክንያት (Point-of-departure) አድርጎ መውሰድ::
    - ልጅን እንደ እግዚአብሔር ስጦታ አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ የኑሮ ሸክም አድርጎ መውሰድ::
    - ልጅ ለመውለድ እየቻሉ ለመውለድ አለመፈለግም::

(ሐ) የመጀመሪያዎች አሥራ አምስት ዓመታት፡-

- የፍቅር መቀዝቀዝ ⇒ መሰለቻቸት (Boredom) ⇒ የሐሳብ አለመግባባት (Communication breakdown)
- የግብረ ሥጋ ግንኙነት እርካታ ማጣት (Lack of sexual intimacy)
- ከሌሎች ቤተሰቦች በተለይም ከሚቀርቡን ቤተሰቦች ጋር በእልክ የመ ድድርና ፉክክር ውስጥ መግባት።

(መ) የመጀመሪያዎቹ ሃያ አምስት ዓመታት፡-

➢ የመካከለኛ ዕድሜ ማለትም÷ ከሰላሳ አምስት እስከ አምሳ አምስት ዕድሜ ያለው ተግዳሮት (Challenge)

- የመልክና የዝና መክሰም (Fading Stage)
- የጤንነት ለውጥ
- የሰውነት መዳከም። (ዓይን÷ ጆሮ÷ጉልበት)
- የባህርይ ለውጥና የሚያመጣውም ስበብ÷ (ቁጣ ⇒ ምሬት ⇒ መዝቀጥ ⇒ የጤንነት መታወክ)
- በሴቶች የወር አበባ መቅረት የሚያመጣው የስሜት÷ የሐሳብና÷ የውሳኔ መዘበራረቅ። (Menopause)

➢ ያልተሟላ ህልም መታወክና ፍርሃት ያመጣል። (Frustration, Fear)

➢ ውድቀትንም ይሁን ድልን ለማስተናገድ አለመቻል።

➢ የገንዘብ ፈተና

- ዝሙት ⇒ የወጣትነት ዘመን ፈተና ነው።
- ገንዘብ ⇒ መካከለኛ ዕድሜ ፈተና ነው።

- ክብር ⇒ የሽምግልና ዘመን ፈተና ነው።

(ሠ) የመጀመሪያዎቹ አምሳ ዓመታት÷

- የወለዱአቸው ልጆች ከእናት ወይንም ከአባት ጋር በማበር በቤተሰብ መሀል የቡድን መንፈስ ሲከስትና÷ አባት ወይንም እናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ብቸኛ ሲሆኑ ብዙ ሥቃይ ያመጣል።
- መሰላሉን የመውረጃ ዘመን ስለሆነ የሚከተሉትን ነገሮች ሊያመጣ ይችላል÷

  - የህሊና ወቀሳ÷ ፀፀትና ተስፋ መቁረጥ
  - ትዕቢት÷ መመጻደቅና÷ የጌታን ክብር መሻማት
  - ወይንም አዲስ የሕይወት ጅማሬ ሆኖ አዳዲስ ራዕዮች እያዩ የሕይወትም ሆነ የአገልግሎት አድማስ የሚሰፋባቸው ዘመናት ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ÷ ነቢዩ ዳንኤል ምዕራፍ 7 ያለው ራዕይ ሲያይ የ68 ዓመት ሽማግሌ ነበር፤ በምዕራፍ 12 ያለውን ሲደመድም የ90 ዓመት ሽማግሌ ነበር። ለዳንኤል የዕድሜ መርዘም የራዕይ መጨመር እንደነበር ልንመለከት እንችላለን።

(ረ) ከአምሳ ዓመታት በኋላ÷ ወርቃማ ዓመታት (Golden Years)

"ጫማና ትዳር ሲያረጅ ይመቻል" እንዲሉ÷ ባልና ሚስት የልጆች ጣልቃ ገብነት ሳይኖራቸው የጠለቀና የነጠረ ፍቅር የሚለማመዱበትና ከመጠን በላይ ደስ የሚሰኙባቸው ዘመናት ናቸው።

- *"ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም÷ ፈሳሾችም አያሰጥሙአት ም፤ ሰው የቤቱን ሀብት ሁሉ ስለፍቅር ቢሰጥ ፈጽሞ ይንቁታል።"* (መኃልየ መኃልየ ዘሰሎሞን 8÷ 7)

- *"በሦስትም የተገመደ ገመድ (ማለትም ባል፥ ሚስትና፥ እግዚአብሔር) ፈጥኖ አይበጠስም።"* (መክብብ 4፥12)

2. የቤተሰብን ዕድገት የሚፈታተኑ ተግዳሮቶች፥ (Challenges)

(ሀ) የደባልነት ኑሮ መኖር፡- (ዘፍ 2፥18 ⇒ ዘፍ 3፥1 ⇒ 4፥4-9)

በባልና በሚስት መካከል የሳላማ ውህደት ሳይኖር የተናጠል ኑሮ መኖር ሲጀመር፤ ኑሮአቸው ሁሉ ድብቅ መሆን ሲጀምር፤ አንዱ በሌላው ዓለም ውስጥ መግባት ሳይችል ሲቀር፤ ግድየለሽነት (Indifference) እየሰፈነ ሲሄድ፤ ባል ወይም ሚስት ለሰይጣን አሠራር/ ማባበል ልባቸውን መክፈት ሲጀምሩ፤ አንዱ የሌላው ጠባቂ መሆኑን ሳያስተውል ሲቀር፤ እንዲያውም የአንዱ ውድቀት የሌላውን ዕድቅ የሚያሳይ/ የሚያረጋግጥ እየመሰላቸው በሌላው ውድቀት ደስ መሰኘት ሲጀምር፤ ኃጢአት በህይወታቸው እየነገሰ፤ ንስሃ ከመግባት ይልቅ ምክንያት በመፍጠር የማምለጫ ቀዳዳ (Scape Goat) ሲፈልጉ፤ ድካምንና ጉስቁልናን አስተውሎ በተሰበረ ልብ ወደ ጌታ ከመቅረብ ይልቅ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ግልድም ማገልደም፥ ኃጢአትን መለባበጥ/ ማስመሰል ሲጀምሩ፤ ሁለት ገፅታ ያለው ጉራማይሌ የሆነ ሕይወት ማሳየት ሲጀምሩ፥ የመንፈሳዊ ሕይወትም ሆነ የትዳር ዕድገታቸውን አደጋ ላይ ይጥለዋል።

(ለ) የባልና ሚስት ያልተመጣጠነ ዕድገት፡- (ዘፍ 18፥9 ፤ 16፥1-6)

ባልና ሚስት በመንፈሳዊ ሕይወት ብስለት፥ ለጌታ ባላቸው ቅርበት፥ በአስተሳሰብ ጥራት፥ በትምህርትና በሌሎች ጥሩ ጉዳዮች ብዛት ያላቸው ልምምድ፥ በአገልግሎት ራዕይና ፀጋ፥ በክርስትናም የሕይወት ዘመንና ልም

ምድ ሳይመጣጠን ሲቀር ዕድገታቸው ሞላላና ሰላላ ይሆናል። ከዚህም ሌላ በትዳራቸው ውስጥ የሐሳብ መጓተት፥ የቋንቋ አለመጣጣምና፥ የሓላማ አለመገናኘት ስለሚያመጣ አለአስፈላጊ የሆነ ስቃይ ይጨምራል። ግለኝነት በቤተሰብ ውስጥ አይሠራም። ባልና ሚስት በሕይወት ጥልቀት፥ በራዕይና በአገልግሎት ፀጋ፥ በትምህርትና በሌሎች ጥሩ ጉዳዮች ያላቸው ልምምድ አብረው ማደግ አለባቸው።

(ሐ) ልጆችን የመለያየት ነጥብ (Point of Departure)

አድርጎ መውሰድ፦ (ዘፍ 25፥19-28)

ባልና ሚስት የወለዷቸውን ልጆች የንግግራቸውና የጭቅጭቃቸው አጀንዳ አድርገው ሲወስዱ፤ ልጆቻቸውንም በሐሳብ ለመለያየታቸው ምክንያት ሲያደርጓቸው፥ በልጆቻቸው መካከልም በአድልዎ አንዱን ወድደው ሌላውን መጥላት ሲጀምሩ፤ ከልጆቻቸው ጋር በተገናኘ በውሣኔ አሰጣጥ፥ በዲሲፕሊን አሰጣጥ፤ ከሌሎች ልጆች ጋር ባላቸው ጥሩ ግንኙነት መለያየትና ማድላት ሲጀምሩ በልጆቹ አዕምሮ ላይ የተጭበረበረ ሥዕል ከመሳሉም በላይ መልኩን የለወጠ ኢሰብዓዊ ድርጊት (abuse)፥ ጭቆናና ግፍ ይሆናል።

(መ) የአባትነት ፀጋ ሲከስም፦ (ዘፍ 37-50)

አባት የክህነት ሥራውን ሲጥል፥ የአባትነት ክብር በቤት ውስጥ ሲደበዝዝ፥ ቤቱንና ልጆቹን በሥርዓት ማስተዳደር ሲያቅተው፤ አመራር በቤተሰብ መሀል ደብዛው ሲጠፋ፤ ሞዴል የሚሆኑ አባትም እናትም እየታጡ ሲሄዱ፤ ልጆች ዓይናቸው የሚያርፍበት ወላጅ ሲያጡ ፤ የቤተሰብ የፀሎት መሰዊያ ሲፈርስ፥ ሕይወት ራሱ ድግግሞሽ መሆን ሲጀምር፥ ከማዕድ ፀሎት ያለፈ እንደቤተሰብ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ የሚያሣልፉት ጊዜ የህልም እንጀራ ሲሆን፤ ቤተሰብ የበላበትን ወጪት ሲገለብጥ፤ ያጎረሰውን የእግዚአብሔርን

እጅ ሲነክስ፣ የጌታን ውለታ የሚያስብበት ሐውልት መስበር ሲጀምር፣ አባት ልቡና ሐሳቡ ከቤት ውጭ ሲወሰድ ለቤተሰብ ትልቅ ተግዳሮት ነው።

(ሠ) ገንዘብን የመውደድ ወጥመድ፦

(ኢያሱ 7÷1-26 ⇒ አካን) (የሐዋ ሥራ 5÷1-11 ⇒ ሐናንያና ሰጲራ)

ባል በገንዘብ ሲፈተን÷ የኃጢአትንም እንጀራ መብላት ሲጀምር፤ ሚስትም ይህን አይታ ከመፀየፍና ባልዋን ከመመለስ ይልቅ የሥርቆት እንጀራ ሲጣፍጣት፤ ወይም ባልና ሚስት በዚህ የሥርቆት ኃጢአት ሲዋጡ÷ ተስማምተውም በጌታም ሆነ በቤተክርስትያን ፊት ማስመሰል ሲጀምሩ÷ በዚህም ምክንያት መርገም ወደቤታቸው መግባት ሲጀምር የእግዚአብሔርም እጅ በነሱ ላይ ስትከብድ፣ ቤተሰቡ በተሠበረ ልብ በተዋረደ መንፈስ በጌታ ፊት ሊቀርብ ይገባዋል። (ሉቃስ 12÷15 ፣ 1ጢሞ 6÷3-11)

(ረ) በቤተሰብ ውስጥ የእግዚአብሔር ምሪት አለመኖር፦

(ሩት 1÷1-6)

እንደ ቤተሰብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይጠይቁ÷ የጌታም ምሪት ሳይኖራቸው÷ ድምፁንም ሳይሰሙ ልባቸው የተመኘውን ማድረግ ሲጀምሩ÷ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ተስፋ ይልቅ በሁኔታዎች ጫና መመራት ሲጀምሩ ፣ ባልና ሚስት እንደ ሜዳ አህያ የምኞታቸው ነፋስ መከተል ሲጀምሩ፣ የጌታ እጅ የሌለበት ጌታም ባልባረከው ከፅድቅም በጎደለ ጉዳይ ላይ ልባቸው መዝቀጥ ሲጀምር፣ ባልና ሚስት በህልም እንጀራ ለመኖር በመንገታቸው ምክንያት በመዝሙር 32÷8-9 እንደተገለፀው በአፋቸው ላይ የመከራ ልጓም እንዲያደርግባቸው ጌታን የሚገፋፉ ሲሆኑ÷ በዚህም ምክንያት የመከራ እንጀራ ሲበሉ በጣም ከባድ ነው።

- ማርያምና ዮሴፍ ጌታን ጥለው መሄዳቸው ጊዜአዊ ዳበሳ እንዲገቡና እን ዲቸገሩ ከማድረጉም በላይ የሦስት ቀን መንገድ እንዲጓዙ አድርጎአቸዋል :: (ሉቃስ 2÷41-52)
- የኤማሆስ መንገደኞች ተብለው የተጠቀሱት ቀልዮጳና ሚስቱም ማርያ ም የጌታ ምሪት ጠፍቶባቸው ተስፋ ስለቆረጡ በትንሣኤ ቀን ወደ ኤማ ሆስ ሲጓዙ እናያቸዋለን:: ዓይናቸው ሲከፈት ግን በዚያኑ ምሽት ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ እናያቸዋለን:: (ሉቃስ 24)

(ሰ) ከእግዚአብሔር ይልቅ ልጆችን ማክበር:-

ከእግዚአብሔር በስጦታና በአደራ የተሰጡን የወለድናቸው ልጆች እያመ ቅንም ሳናውቅም ከጌታ የበለጠ እንደጣኦት ልናመልካቸው ስንጀምርና፣ በእ ኛና በእርሱ መካከልም ግርዶሽ እንዲሆኑ ስንፈቅድላቸው የእግዚአብሔር መንፈስ እየተሸበሸበ ይመጣል:: (1ሳሙ 2÷29-30 ⇒ ኤሊ፤ ማር 6÷16-29 ⇒ ንጉሥ ሄሮድስ)

(ሸ) በአገልግሎት ሰበብ ቤተሰብን መጣል:-

(1 ሳሙኤል 8÷1-5 ፤ 2÷11-36)

የቤተ ክርስትያን አገልጋዮች በአገልግሎትና በስብሰባዎች ብዛት ምክንያ ት ቤተሰቦቻቸውን እየጣሉ ሲመጡ፣ ቤቱን በአለት ላይ ሳይሆን፥ በአሸዋ ላይ እንደሠራ ሰውን ይመስላሉ:: (ማቴ. 7÷ 24-27)

(ቀ) የነቢይነት ህይወት መኖር አለመቻል:-

(ዘፍ 19÷1-28 ⇒ ሎጥ ፤ ዘፍ 13÷10 ፤ 2ጴጥ 2÷7-8)

ቤተሰብ የነቢይነት ሕይወት መኖር ሲያቅተው፣ በኑሮው ኃጢአትን መኮነን ሲያቅተው፥ የፅድቅና የቅድስና ጫና ማምጣት ሲሳነው፤ "*ሙሻ ወደ*

ትፋቱ ይመለሳል" እንደተባለ ልቡ ሁልጊዜ ጥሎት ወደመጣው ዓለማዊነት ሲጥመነመን፤ እግዚአብሔርን መፍራት ጭንቅ ሲሆንባቸው ሁልጊዜም ራሳቸውን መስቀለኛ መንገድ ላይ ሲያገኝ፤ የቤተሰብን መለኪያ በማመቻመች (Compromise) መጣስ ምንም ሳይመስለው መሆን እንዳለበት አድርጎ መውሰድ ሲጀምር ቤቱ እየዘመመ ይመጣል። (በአሸዋ ላይ እንደተሠራ ቤት⇒ ማቴ 7÷ 24-27)

(በ) **የአክዓብና የኤልዛቤል ኑሮ መኖር፡-** (1ነገ 16÷29-34)

ክርስትያን ወንድም/ እህት እያወቁ የጌታን ቃል በመጣስ (2 ቆሮ 6÷ 14 18) ከማያምን ሰው ጋር በጋብቻ መቆራኘት፡ ዓለማዊነትን በቤት ማስተናገድ÷ ውሉ የማይታወቅ ቅይጥና ጉራማይሌ/ ዝንጉርጉር ኑሮ መኖርና÷ ክርስትያኑ በዓለማዊው እጅ እንዲወድቅ ያደርጋል። (1ነገ 22÷ 1ff)

3. የክርስትያን ቤተሰብ ዕድገት ምክንያቶች÷

(ሀ) የአባት ክህነት በቤት ውስጥ መልክ ሲይዝ፤ አባት ወደቤት ሲመለስ፤ የፀሎት መሰዊያ በቤተሰብ መሀል መሥራት ሲጀምር፡ አባት በአመራሩ ሞዴል ሲሆን፤ (ዘፍ 8÷ 20-21፤ 13÷ 18-19 ፤ ኢያሱ 24÷ 15)

(ለ) እንደ ቤተሰብ ለእግዚአብሔር ሥራ መሰጠት÷ ማገልገል በማይቻልበት ሁኔታ እንኳን ሳይቀር ህይወትን መሥዋዕት እያደረጉ ማገልገል፤ (1ነገ 18÷ 3-4 ፤ 12-13 ፤ 2ነገ 4÷ 1-7)

(ሐ) የቤተሰብ ልብና ቤት የእግዚአብሔርን ሰዎች ለመቀበልና ለማስተናገድ የተከፈተ ሲሆን÷ የጌታን ሥራ በሥውር መደገፍ ሲችሉ÷ የእግዚአብሔር መንግሥት አጀንዳ ገብቷቸው ቤታቸው÷ ንብረታቸው÷ ህይወታቸውን ለመስጠት እየተመካከሩ በአንድ ልብ ማድረግ ሲችሉ፡ የእግ

ዚአብሔር ልብ በእነርሱ ማረፍ ሲጀምር፥ የቅዱሳንም መንፈስ በእነር ሱ ምክንያት ሲታደስ፤ (2ነገ 4÷ 8-37 ፤ ፊልሞና 2፤ 7 ፤ አቂላና ጵርስ ቅላ ሮሜ 16÷ 3-4 ፤ 2ጢሞ 1÷ 15-18)

(መ) የትዳር ጓደኞቻችንን ድካም መሸፈን፤ የትዳር ጓደኛችን ስለ እግዚአብ ሔር አሠራር ያለው/ ያላት እውቀት እያደገ እንዲመጣ በትዕግሥት ጸንተን ለዕድገታቸው ምክንያት መሆን፤ የመረዳታቸው መጠን ያነሰ ቢመስልም በሚገባቸው መንገድ የጌታን አመራር ማሳየት፥ ማበረታታ ት፥ ባለማቋረጥ ስለእነርሱ መጸለይ። (የማኑሄ ቤተሰብ፡- መሳፍንት 13 ÷2-25 ፤ የናባል ሚስት አብግያ 1ሳሙ 25÷9-38)

(ሠ) ቤተሰብ የነቢይነት ህይወት (Prophetic Life) መኖር ሲችል፥ በሚኖሩ ት ኑሮ ኃጢአትን መፀየፍም ሆነ መኮነን ሲችሉ፥ እነሱና ልጆቻቸው በእግዚአብሔር ጥልቅ አሠራር ውስጥ ሲገቡ፥ ከተራ ህይወትና ኑሮ ወጥተው ላቅ ያለ መንፈሳዊ ሕይወት ሲኖሩ፥ ያሉበትን ትውልድ በቅን ነትና እግዚአብሔርን በማስከበር አገልግለው ሲያልፉ፤

- (ያሬድ⇒ ሄኖክ ዘፍ 5÷21-24 ፤ ኢሳ 8÷18 ፤ የሐዋ ሥራ 21÷ 7-10 ⇒ የሐዋ ሥራ 13÷36)

(ረ) የመከራን ዘመን ጌታን በመታመንና በትዕግሥት እንደቤተሰብ ማለፍ፣

- (ያዕ 5÷7-11፤ ኢዮብ 1÷21-22 ፤ 2÷9-10፤ ኢሳ 50÷10-5÷2)

(ሰ) እንደቤተሰብ በማይቻል ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔር ታላቅና ያል ተጠበበትነውን ነገር ሊያደርግ ይችላል ብሎ መታመን፥ (Hope against Hope)

- (አብርሃም፡- ሮሜ 4፥17-22 ፤ ኤልሣቤጥና ዘካርያስ፡- ሉቃስ 1፥ 1-25)

4. ግጭትን መፍታት በክርስትያን ቤተሰብ፥

ኤፌ 4፥25-32

(ሀ). የግጭት ምክንያቶች፥

1. መሠረቱ የተበላሸ ሲሆን፥

   - ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ባለማወቅ ወደትዳር ሲገቡ፥
   - ከግል ስሜት፡ ከቤተሰብ ጫና የተነሣ ማግባት እንዳለባቸው መስሎአ ቸው ሲጋቡ፥
   - ሞላላና ሰላላ የክርስትና ህይወት ሲኖራቸውና መንፈሳዊ ሕይወታቸ ው የማይመጣጠን ሲሆን፥

2. የመጣጣም ጊዜ (Adjustment Period) አላስፈላጊ በሆነ መንገድ ሲራዘም (Prolonged Stress)

3. በወላጆች መካከል በልጆች አስተዳደግና ዲስፕሊን አለመጣጣምና መለያ የት በሚኖርበት ጊዜ፥

4. የወላጆችና የአጠቃላይ ቤተሰብ (Extended Family) ጣልቃ ገብነት በባለ ትዳሮቹ መሃል ሲከሰት፥
   - ለወላጅ የሚደረግ ድጋፍ ለአንደኛው ወገን ስውር ሲሆንና በመካከላ ቸውም ግልፅነት ሳይኖር፥
   - ወላጆች በልጅ ልጆች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሲኖራቸው፥
   - ወላጆችን ከትዳራቸው የበለጠ ማመለክ ሲጀምሩ፥

5. ከተወለዱበት ቀየ/ ገጠር÷ ትንሽ ከተማ÷ ወይንም አገር ለቆ ወደሌላ ትልቅ ከተማ ወይንም አገር ሄዶ መኖር መጀመር (Migration/ Immigration Problems)

- ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ቶሎ አካባቢን የመልመድ ችሎታ አላቸው። ከዚህ የተነሳ ባሎች መቅናት ይጀምሩና በባልና በሚስቱ መካከል መጓተትን ይፈጥራል። ምሳሌ: ተራ ሥራ ለመሥራት÷ የኩተማውን ወይንም የአገሩን አሠራር (system) ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ፈጥነው መልመዳቸው፤
- በከተሜነትና በዘመናዊነት ምክንያት የነበረን ሰብዓዊ ክብር በመነካቱ ምክንያት የውስጥ ቁስል ይፈጥራል።
- በባህል ለውጥ ምክንያት የሚፈጠር የሕይወት እንግዳ ጋጭ (Cultural Shock) ⇒ የምንኖርበትን አገር ባህል መልመድ (Adjust ment) ⇒ የራሳችን ባህል ከምንኖርበት አገር ባህል ጋር ማዋሃድና ማጣጣም (Assimilation)
- ብቸኝነት (Loneliness: being lost in the crowd)
- ያደግንበት ማሕበራዊ ኑሮ ግለኝነት ከሞላበት ባህል ጋር ሲጋጭ (Community Vs Individualism)
- ዘመናዊነት÷ ከተሜነትና÷ የግል ኑሮ በሕይወት ዘይቤአችን ላይ ተጽዕኖ ማምጣት ሲጀምር (Modernity, Urbanization, Private Life Vs Public Life)

6. የሥራና የኑሮ ውጥረት

- "እግዚአብሔር ራሳቸውን የሚረዱትን ይረዳል" እና "ነገሮች ለተሳኩለት ስኬታማ ይሆናል" ("Success to the successful!") የሚል የተሳ

ሳተ አመለካከት መያዝ ሕይወታችን የተመሳቀለና የተወዛገበ ያደርገዋል።

- ብዙ ሰዓት መሥራት ⇒ ቤተሰብን መስዋዕት ማድረግ ⇒ የቋንቋ/ የሐሳብ አለመግባባት (Communication Breakdown) ⇒ አለአስፈላጊ ግጭት (Conflict) ⇒ ቁጣ (Anger) ⇒ መራራነት (Bitterness) ⇒ የመንፈስ ዝቅጠት (Depression) ⇒ በሥጋ ደዌ/ በሽታ መታመም (Body Sickness)

7. የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አለመጣጣም/ እርካታ ማጣት፣ ወይንም የአልጋ ንጽህና ማጣት

- አንዱ ምክንያት የሕይወትና የኑሮ ጫና/ ጭንቅንቆሽ መብዛት የግብረ-ሥጋ ግኑኝነታችንን ያዳክመዋል።
- ስለ ግብረ-ሥጋ ጉዳይ የተመጠነ፣ ወይንም ምንም እውቀት፣ ወይንም እጅግ የተሳሳተና የተዛባ አመለካከት ሲኖረን የግብረ-ሥጋ ግንኙነታችን መጣጣም እንዳይኖረው ያደርገዋል።

(ለ). የባህርያት ልዩነት አለማወቅ፣ (Temperments)[79]

በባለ ትዳሮች ይሁን በሌሎች ሰብዓዊ ግንኙነቶች መካከል ለብዙ ግጭቶች መነሣት ምክኒያት አንዱና ዋነኛ ነገር የራሳችንም ሆነ የሌላው ሰው ተፈጥሮአዊ ስብዕናና (Persoanlity) ባህርይ አለማወቃችን ነው። በሰዎች ግንኙነት ውስጥ የአፈጣጠርም ሆነ የባህርያት ልዩነት እንዳለ አለማወቃችን አንዳችን ከሌላችን አለአስፈላጊ እውነተኝነት የሌለው መጠባበቅ (Unrealistic Expectation) እንዲኖረን ከማድረጉም በላይ፣ የጠበቅነው ባህርይ ሳናገኘው ስንቀር ደግሞ ቅሬታን፣ የልብ ሐዘንን፣ አልፎም ቁጣን፣ ምሬትን፣ የመንፈ

---

[79]ሰፋ ላለ ጥናት የሚከተለውን መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል፣ Tim LaHaye, *Spirit-Controlled Temperament*, (London: Coverdale House, 1972); Ibid., Wheaton: Tyndale House, 1966.

ስ ዝቅጠትንና÷ የሥጋ በሽታን ያመጣብናል። ከዚህም የተነሳ አራት ዓይነት ባህርያት እንዳሉና የነዚህም ባህርያት ብርታትና ድካም ከዚህ በታች ለማየት እንሞክራለን።

- **እግዚአብሔር የፈጠረውን ስብዕናችንን ሳይሆን÷ ባህርያችንን ይለውጣል! God never changes our personality; but He changes our Character!**

(1) **ብርታታቸው÷**

1. **የሳንጉዊን ጠባይ ያላቸው÷ (The Sanguine)**
   - በሕይወት ረክተው መኖር ይችላሉ
   - ለማወቅ ጉጉት አላቸው
   - የተደረገባቸውን ክፉ መርሳት ይችላሉ
   - ነገ ለእነሱ ብሩህ ነው
   - ከእግዚአብሔር የተሰጠ ችሎታ አላቸው
   - የትናንቱን እየረሱ ዛሬን መኖር ይችላሉ
   - የነገ ነገር አያስጨንቃቸውም
   - በትንሽም ሆነ በትልቁ ደስ ይላቸዋል
   - አዳዲስ ፕላን ማውጣት ይቀናቸዋል
   - በቀላሉ ወዳጆችን ማፍራት ይችላሉ
   - በጣም ርህሩሆች ናቸው።

2. **ኮለሪክ ጠባይ ያላቸው÷ (The Choleric)**
   - ግላዊ ዲሲፕሊን አላቸው
   - በራሳቸው ችሎታ ይታመናሉ
   - ተጋፍተው መሄድ ይችላሉ
   - በሆነ ነገር መርጋት አይችሉም

- ሆኖም በደንብ ማቀድ ይችላሉ
- ሰዎችን ላሰቡት ዓላማ የማስተባበር ችሎታ አላቸው
- የትኩረትና የዓላማ አቅጣጫ አላቸው
- ነገሮች በሥራ እንዲተረጎሙ ያደርጋሉ
- ውሳኔ አሰጣጣቸው በቀልብ ሳይሆን በጭልጥታ ነው
- የአመራር ችሎታቸው ከፍተኛ ነው
- ጽኑ ፈቃድ አላቸው÷ አንድን ቡድን መጫን ይችላሉ
- አጣዳፊ ጉዳይ ሲያጋጥም ጽናት አላቸው
- እነርሱ ለሚያደርጉት ነገር ሰዎች ምላሽ ይሰጣሉ
- ነገ ለእነርሱ ብሩህ ነው
- ፊት ፊት መሄድ ይቀናቸዋል
- የሚያመጣውን አደጋ/ ችግር አይታያቸውም
- ለማየት የሚፈልጉት መልካሙን ብቻ ነው
- በቀላሉ የማይናወጥ ብርታት አላቸው::

3. **ሜላንኮሊ ጠባይ ያላቸው÷ (The Melancholy)**
   - በቀላሉ የሚሸበሸቡ/ ስብስብ የሚሉ ናቸው
   - የማሰብ ችሎታ አላቸው
   - ምላሽ ሲሰጡ በስሜታቸው ነው
   - አንድን ነገር የማሰላሰለል/ የማውጠንጠን ችሎታ አላቸው
   - በፈጠራ ማሰብ ይችላሉ
   - ፍፁምነትን ይጠብቃሉ
   - ሰውን በቀላሉ አይቀርቡም÷ ሆኖም ጥሩ ጓደኛ መሆን ይችላሉ
   - ችግር ሲፈጠር ሐሳብ ማመንጨት ይቀናቸዋል
   - የተሰጣቸውን ሥራ መጨረስ የሚችሉ ናቸው
   - በሰው ዓይን የማይታይ ሥራ መሥራት ይቀናቸዋል
   - የራሳቸውን ውሱንነት በሚገባ ያውቃሉ
   - በቀላሉ ከሰው ጋር መደባለቅ አይቀናቸውም

- የሚፈልጉትን ነገር ለመናገር አይቸገሩም::

4. **የፊለግማቲክ ጠባይ ያላቸው÷ (The Phlegmatic)**
   - ሰዎችን የማሳቅ ችሎታቸው የሚያስደንቅ ነው
   - በጣም ጥሩ ምክር ሰጪዎች ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው
   - በጣም ቀዝቃዛና ቀሰስተኞች ናቸው
   - በቀላሉ ከሰው ጋር መናበስ ይችላሉ
   - ጥሩ አድማጮች ናቸው
   - ሁኔታን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ሊያዩ ይችላሉ
   - ራሳቸውን ከሰው ጋር ማመሳሰል የሚችሉበት ችሎታ አላቸው
   - ሰው ሊታመንባቸው የሚችሉ ናቸው
   - የታመኑ ጌደኞች መሆን ይችላሉ
   - ታማኞች ናቸው
   - ፍሬአቸውን በሥራ ይገልጻሉ
   - ሁኔታዎችን ማጤን ይችላሉ
   - በደንብ መሥራት የሚችሉት በጫና ውስጥ ነው
   - የጠራ ሥራ መሥራት ግን ይችላሉ
   - ፍጹምነት ባይጠብቁም÷ ለሚሠሩት ሥራ ግን ከፍ ያለ መለኪያ አላ ቸው
   - አካሄዳቸውንና አወጣጣቸውን መገመት ይቻላል::

(2) ድካማቸው÷

1. **የሳንጉዊን ጠባይ ያላቸው÷ (The Sanguine)**
   - የረጉና የሰከኑ አይደሉም
   - ደካማ ፈቃድ ስላላቸው በአንድ ነገር ላይ መርጋት አይችሉም
   - አንድን ነገር በመጀመር በጣም ጎበዞች ናቸው÷ ሆኖም የጀመሩትን ለመጨረስ ግን ዲሲፕልን የላቸውም
   - ላደረጉት ነገር መመሥገን የሚወዱ ናቸው

- ስሜታቸው የረገበ ስላልሆነ የተረጋጉ አይደሉም::

2. **የኮለሪክ ጠባይ ያላቸው÷ (The Choleric)**

- በቀላሉ የሚቆጡና የሚናደዱ ስለሆኑ ከሰው ጋር ያጋጫቸዋል
- በጣም ጨካኞች ናቸው
- ያቀዱትን ነገር ለመፈጸም ሲሉ ህግን ለመጣስም ይሁን÷ የተጥመዘመዘ መንገድ ለመሄድ ወደኋላ አይሉም
- ላጠፉት ጥፋት ይቅርታ ለመጠየቅ ይቸገራሉ
- አጥንትን የሚሠብሩና ስሜትን የሚጎዱ የአሽሙር ንግግሮች ይናገራሉ
- በራሳቸው ስለሚታመኑ በእግዚአብሔር ላይ ለመታመንና ለመደገፍ አይችሉም::

3. **የመላንኮሊ ጠባይ ያላቸው÷ (The Melancholy)**

- ሁሉም ነገር ከራሳቸው ጥቅም አንፃር ብቻ ያያሉ እንጂ÷ ለሌላው ሰው የሚያመጣውን ሰበብ ማየት አይችሉም
- ስለነገ ሲያስቡ ለእነርሱ ምንም ጊዜም ቢሆን ጨምዳዳ ነው
- ተለዋዋጭ ስሜት ስላላቸው አብሮአቸው ለሚኖር ሰው ግራ ያጋባሉ
- ለተደረገባቸው በደል ነው ብለው ለሚያስቡት ነገር ሳይበቀሉ አይመለሱም::

4. **የፈለግማቲክ ጠባይ ያላቸው÷ (The Phlegmatic)**

- በጣም ቀስ‌ስተኞችና ሰነፎች ስለሆኑ እግዚአብሔር የሰጣቸው ዕዳሎት የሞላበት ጊዜና ዘመን በከንቱ ሊያልፍባቸው ይችላል
- በሌላ ሰው ላይ መቀለድ ይቀናቸዋል
- ሐሳበ ደረቆችና ግትሮች ናቸው

- ሰውን ለማስቀየም ስለማይፈልጉ ውሳኔ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ሁል ጊዜ ይዋልላሉ::

  ❖ ቁጣ ሁለገብና ዓለም አቀፍ ወይም ሁሉ አቀፍ ታጢአት በመ ሆኑ የተጠቀሱትን ባህርያት በሙሉ ያገናኛል::

  ❖

5. የግጭት ዓይነቶች÷

(ሀ). ሦስት ዓይነት ችግሮች አሉ÷

- የውስጣዊ አስተሳሰብ ችግር (Attitude Porblem)
- የአፍ አላፊ/ በአንደበት መሳት የሚመጣ ግጭት (Verbal Problem)
- ሆነ ተብሎ የሚደረግ የክፋት ድርጊት ችግር (Action Problem)

(ለ). ግጭትን ለመፍታት የግጭቱን ዓይነት መወሰን÷

	ፍ ላ ጎ ት		
ባ ህ ር ይ		የማይጣጣም	የሚጣጣም
	የማይጣጣም	እውነተኛ ግጭት	የውሸት ግጭት
	የሚጣጣም	ድብቅ/ ስውር ግጭት	ግጭት የሌለው ግንኙነት

በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት የባልና የሚስት ባህርይና ፍላጎት የማይጣጣሙ በሚሆንበት ጊዜ በመካከላቸው ያለው ግጭት እውነተኛ ግጭት ይሆናል:: በባህርያቸው የማይጣጣሙ ሆነው÷ የፍላጎት ግጭት ከሌላቸው ግን ግጭታቸ

ው የውሸት ግጭት ነው። በባህርያቸውና በፍላጎታቸው የሚጣጣሙ/ የሚስማሙ ከሆነ ደግሞ የሠመረ ግንኙነት ስላላቸው ግጭት የለሽ ግንኙነት ይሆናል ማለት ነው። ከእነዚህ ሁሉ አደገኛው ግን በባህርያቸው የሚጣጣሙ ሆነው፥ አንዳቸው የሌላውን ስብዕና ለመቅደድ ወይም የባልን/ የሚስትን በቤተሰቡ ያለው ድርሻ፥ ሚናና ኃላፊነት ለማሳነስ ስውር፥ ረቂቅና፥ በማይታወቅ መንገድ ለመጉዳት የሚያደርጉት የክፉት ሥራ በሚኖርበት ጊዜ በመካከላቸው ያለው ግጭት ድብቅ/ ስውር ግጭት ይሆናል። እንዲህ ባለ ሁኔታ የተጎዳው ባል ወይም ሚስት ጉዳዩን ወደ ብርሃን አውጥቶ ነገሩን ጠረጴዛ ላይ አድርጎ በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ ውስጥ ሆኖ በለዘበና ፀጋ በተሞላበት አንደበት ከትዳር ጓደኛው ጋር መነጋገርና በይቅርታና በምሀረት ችግሩን መፍታት ይገባል።

(ሐ). የግጭት መፍትሔ፥

1. በዝምታ መዋጥ (Unhealthy silence)
2. ሌላውን መጫን (Imposing)
3. አላስፈላጊ መገዛት (Yielding)
4. ማመቻመች (Compromising)
5. **ግጭትን መፍታት፥ እንኳር በሆነውና ደቃቅ በሆኑት አነጋጋሪ ጉዳዮች መካከል መለየት (Differentiate between the major issues and the minor issues)**

   ❖ በእግዚአብሔር ፊት እንደተቀመጡ ሰዎች፤ መደማመጥ ባለበት ሁኔታ (atmosphere) መነጋገርና ችግሩን ከጸሎት ጋር መፍታት።

6. እንደ ቤተሰብ ችግራችንን ለመፍታት ስንነጋገር የሚከተሉትን አስፈላጊ ነገሮች ልብ ልንል ይገባል።
   ❖ በባል ወይንም በሚስት ላይ ከማተኮር ይልቅ ባለያየን ጉዳይ ላይ ማተኮር (Focus on issues, than personalities)

- ❖ የምንነጋገርበትን ችግር በአንድ ላይ ሆነን ማየት (Face the issues together!)
- ❖ ምንም ጊዜ ቢሆን ውይይቱን የሁለታችን እንጂ የአንድ ሰው ንግግር አናድርገው (Don't make it monolog; rather make it dialogue and discussion)
- ❖ በተቻለ መጠን ውይይታችን ግልፅነትና፥ እውነትን የተሞላና ሚዛኑን የጠበቀ እናድርገው። መለባበጥንና መሸፋፈንን፥ እንዲሁም ፈራጅ የሆነም መንፈስ እናስወግድ። (Make it open, honest, and objective; avoid cover-ups! And Judgmental Spirit)
- ❖ አንዴ ተነጋግረን ይቅርታ የተጠያየቅንበትን ጉዳይ መልሰን መላልሰን አንነጋገርበት። (Don't file issues) (ኤፌ 4÷27)
- ❖ በፍቅራችን ውስጥ እውነት ይኑርበት፥ በእውነታችንም ውስጥ ፍቅር ይኑርበት። (ኤፌ 4÷15)(ፊል 1÷11)

ሁልጊዜ የሚከተሉትን ነገሮች ልብ እንበል፥

- በእግዚአብሔር ፊትና በእግዚአብሔር ጉባዔ ፊት የገባነውን ቃል ኪዳን እናስብ።
- ከጌታ የተሰጡንን ልጆቻችንንና ትውልዳችንን እናስብ።
- እንደ እግዚአብሔር ቃል ማሰብና መወሰን እንዳለብንና የክርስትና ምሥክርነታችንን እንጠብቅ።
- ባላችን ወይንም ሚስታችን በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራቸውንና የከበሩ መሆናቸውን እናስብ።

ለግልና ለቡድን ውይይት የሚረዱ ጥያቄዎች፥

1. ሰይጣን በጋብቻና በቤተሰብ ላይ የሚያመጣቸው መንፈሳዊ ውጊያዎች ምንድናቸው?

2. በኤፌሶን መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን የሐዋርያው ጳውሎስ አንኳር ሐሳቦች ዘርዝር::

3. ሐዋርያው ጳውሎስ ሰይጣን በቤተሰብም ሆነ በአጠቃላይ በአማኞች ላይ የሚያመጣው መንፈሳዊ ውጊያ ከምን ዓይነት ሐሳቦች አንጻር እንድናየው የፈለገ ይመስልሃል?

4. ሰይጣን በቤተሰብ ላይ የሚያመጣቸው ሦስት ፈተናዎች ምን ያህል እውነትነት አላቸው ትላለህ?

5. እንደ ግለሰብም ይሁን እንደ ቤተሰብ መንፈሳዊ ውጊያን በሚገባ ለመዋጋት የሚረዱ የተሰጡት የመፍትሔ ሐሳቦች ዝርዝር::

6. በኤፌሶን 6፥ 10-20 የተገለፁትን ሐሳቦች በማሰላሰል የተማርካቸው ነገሮች ግለፅ::

7. በየዘመኑ በቤተሰብ መካከል የሚነሱትን ችግሮች ለመፍታት ልንከተላቸው የሚገቡን መመርያዎች ምን ምንድናቸው?

8. የበደለንን የትዳር ጓደኛ ይቅርታ ማድረግና የተበደልነውን ነገር መርሳት የቤተሰብም መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ጤንነት ለመጠበቅ ምን ያህል አስተዋፅዖ አለው ትላለህ?